# ግርዶ

ደራሲ ፉአድ ሙኛ



## ክፍል አንድ (1)

ጠዋት ነው፡ ገና ጥቂሩ ክር ከነ ጨክር በቅጡአልተለያየም ፡ ሰሚር የቤቱን በር በሀይል በርግዶ ወጣ ፡ ፊቱ ላይ ንዴት ይንቀለቀላል፡ ፡ የሰለቸው፣ ተስፋውየ ተሟጠጠሚሆኑ ከፊቱ ላይ በደማቁ ይነ በባል፡ ፡ ገና ከእንቅልፉ እንደተነ ሳ የሚስቱ የ ሚያባርቅ ድምፅ ለቀን የሚበቃውን ማከፋት አደለው ፡ ማከፋት እድል አይደለምእንጂ ይህን ሰሞን በጠዋቱ አሊያምማታ ከስራ ሲማለስ የሚስቱን አጥንት ሰርሳሪ ምላስ ይታደላል፡ ፡ ገና ከእንቅልፉ ተነ ስቶ ሳይጨርስ ‹‹አንተ አሁን ምንህ ወንድ ነው? ለማን ጠልጠሎማአህያምአንጠልጥሏል!›› አለቸው፡ ፡ የፀባይዋ መቀየር ግራ እየገባውዝም ሲላት ‹‹ስማያንተ ደመውዝ እኮ እንኳን ለትዳር ለአዳር አይሆንም ፡ አንቀባርሬ ባኖርኩህ እንደ ወንዶቹ መንቀባረር ያምርሀል እንዴ? ከንቱ!›› ብላ ደመን አፈላቸው ፡ ስትናገር ሌላ ብሎክ ያሉ የኮንደሚ የሙን ዋሪዎች እስኪሰሙድረስ እየ ጮኸች ነው ፡ እንደለመደውተነ ስቶ በሩን በርግዶ በቅጡሳይለብስ የሚስቱ አዲስ ፀባይ ግራ እየገ ባውማስጂድ ሄዶ ከሰገደ በኋላ ከኮንደሚ የሙትንሽ ወጣ ብሎ ወዳለውየጓደኛውቤት ሄደ፡ ፡
ሰሚር እና ዩሱፍ ከልጅነ ት ጀምሮ አብሮ አደግ ናቸው ፡ ሁለቱምየሀያ አምስት አመት ወጣቶች! ሰሚር እነ ዩሱፍ ቤት ሲደርስ ዩሱፍ የንጋት ስግደት ሰግዶ ሲማለስ በር ላይ ተገናኙ፡ ፡ ቤት ገብተው እንደተቀማጡዘቢባ ትኩስ ወተት ይዛ እየተፍለቀለቀች አቀረበችላቸው ፡ ሰሚር ፈገግ ብሎ ‹‹አሁንምእንደ ህፃን ከወተት ውጪአይጠጣምአይደል? ለምን በጡጦ አትሰጪውም?›› አለ፡ ፡ ዘቢባ ፈገግታዋ እንዳበበ ወተቱን አቅርባላቸውወጣች፡ ፡
ሰሚር ዩሱፍን ፍዝዝ ብሎእያየው‹‹ያፊ ግን ዘቢን ለምን አታገባትም?›› አለው ፡ ዩሱፍ ከተቀማጡበት አረቢያን መጅሊስ በሩ ጋር ወዳለውማጋረጃ አይኖቹን አሻግሮ ወርውሮ በዝምታ ከተዋጠ በኋላ ‹‹ይሄን ጥያቄ ለምን እየደጋገምክ እንደምትጠይቀኝ ግራ ነ ውየሚ ባኝ! የአጎቴ ልጅ ናት ብዬ ላንተ መናገር አለብኝ እንዴ?›› አለ።
‹‹አንተ ቆይ ሀይማኖተኛ ነ ኝ ትል የለ እንዴ? የአጎት ልጅ ማግባትን ማ ውክልክል ያደረገ ው?››
‹‹ባሕላችን ነ ዋ! ባሕላችን! እነ እቴቴ ዘቢባን ላግባ ብል አይኔ ን እንኳ ለማየ ት ፈቃደኛ የሚሆኑ ይማስልሀል?›› ብሎጀርባውን መጅሊሱ ላይ ሲያደላድል የሰሚር ስልክ ጠራ፡ ፡ ኹሉድ ነ በረች! ሚስቱ! አሁን እንደዛ ውሻ አድርጋ ሰድባውአሁን ስትደውልለት ፈገግ ለማለት እየሞከረ የቀረውን ስድብ ለመቀበል ስልኩን አነ ሳ፡ ፡
‹‹ደሞምን ቀረሽ?››
‹‹ምን ማለት ነ ው? ቁርስ እኮ ሳትበላ ነ ውየ ወጣኸውምን ሆንክብኝ?››
‹‹አንደኛ አላጋጨሆነ ሽ የለ እንዴበአላህ? ለምን አትወዳደሪም?››
ባኮረፈ ድምፅ ‹‹ሁቢ አታናደኝ! ደሞበጠዋት ቻውሳትለኝ ፣ ቁርስ ሳንበላ ወጥተህ ልትቆጣኝ ትፈልጋለህ እንዴ? ወላሂ አሁኑኑ ና!›› ብላ ተሰናብታውስልኩን ዘጋቸው ፡ ወላሂ ካለች አለች ነ ው ፡ የምሯን ነ ው ፡ ሰሚር ግራ ግብት ብሎት በትካዜ ውስጥ ጠፋ፡ ፡ ዩሱፍ የሰሚርን ሁኔ ታ እያየ ‹‹ግን ከኹሉዴጋር ሰላምናችሁ? እንደድሮውከጎኗ አለመጥፋት ፣ ስለሷ አውርቶ አለመጥገብ ምና ምን እየተውክ ነ ው ፡ ብቻ ለውጦች ያየ ሁብህ ማስሎኛል፡ ፡ ›› አለ፡ ፡
ሰሚር ወደ ዩሱፍ ማኑ ለማኑ ዞረና አይኖቹ አሁንምሩቅ እያዩ ‹‹ያፊዬ ታውቃለህ ኹሉዴ ሁለት ሰው እየ ሆነ ችብኝ ነ ው ፡ የሆነ ሰዓት ላይ በጣምታዋርደኛለች፡ ፡ የማላውቃት ኹሉድ ትሆናለች፡ ፡ ከዛ ደግሞሜልሳ ምንምእንዳልተፈጠረ ትሆንና የሚውቃትን አፍቃሪና ተንከባካቢዋን ኹሉድ ትሆናለች፡ ፡ ጠዋት በጣምአሜራኝ ነ በር አንተ ጋ የ ማጣሁት። አሁን ደግሞደውላ ቁርስ እንብላ ፣ ቻውሳትለኝ ለምን ሄድክ ትለኛለች፡ ፡ ግራ ነ ውየ ገባኝ ግራ!›› አለ፡ ፡
ዩሱፍ ፈገግ እንደማለት እያለ ‹‹ ያውፍቅሯን በእንክብካቤ ብቻ ከማየ ት አንዳንዴ ለየ ት ባለ ሜሌኩ



Comment [1]:

ልትገልፀውፈልጋ ይሆናላ!›› አለ፡ ፡
‹‹ትቀልዳለህ እንዴ? የምሬን እኮ ነው! በጣምተቆጥታ ምናምን ነው

የምትሰድበኝ እኮ! በኋላ ደግሞወደ ሜላዓክነቷ ትማላሳለች፡ ፡ ››
‹‹ምክንያቷን ጠይቀኻት ታውቃለህ?››
‹‹ አይ አልጠየቅኳትም›
‹‹ምን ያህል ጊዜ ይሆናል ይሄን ፀባይ ካመጣች?››
‹‹ወር ሊሆነ ውነ ውማሰለኝ!››
‹‹አርግዛለች እንዴ?››
‹‹እኔ ንጃ!››
ወሬያቸውን ሳያሳርጉ የዩሱፍ ታናሽ እህት ዩስራ እየተፍነ ከነ ከች ገባች፡ ፡ ዩስራ የአስራ ስምንት አመት አበባ ናት፡ ፡ ቅጠፉኝ ቅጠፉኝ የምትል የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተሚ! ሲበዛ ተጫዋች ናት፡ ፡ በእጇ በስቴፐላር የተያያዙ ትኬቶችን ይዛለች፡ ፡ ዩሱፍ ፈገግ እያለ ‹‹ወይኔ በአላህ ይሄ የፈረደበት ትኬት ማጣደግሞ!›› አለ፡ ፡ ዩስራ ፈገግ እንዳለች ከዩሱፍ አጠገብ ተቀማጠችና ‹‹ወሬ አታብዛ! የዛሬ ሳምንት እሁድ ገራሚየ ነሺዳ አልበምይሚ ቃል፡ ፡ በአላህ የመግቢያ ትኬት ግዙኝ!›› አለች፡ ፡
የከተማውማሰል ዝግጅቶችን መግቢያ ካርድ የፈለገ ሰውዩስራ ጋር አያጣም ፡ በየቦታውሁሉ እሷ አለች፡ ፡ ዩሱፍ እየተነ ጫ ጨአራት የመግቢያ ትኬቶችን ገዛት፡ ፡ ሰሚር አሁንምከትካዜውጋር ይታገላል፡ ፡ በአይኖቹ ኹሉድን ወዳገባበት የሠርጉ ቀን የኋሊት ይጋልባል፡ ፡ ኹሉድ የቀይ ዳማዋ በጉንጯስርጉድ የተኳለውፈገግታዋን እያፈሰሰች ‹‹ያንተ ልሆን ነውእኮ›› ስትለውበሀፍረት አንገቱን የደፋበትን ቀን ያስብና ደስ ይለዋል፡ ፡ በህይወቱ እንደዛች ቃልና እንደዛ ቀን ያስደሰተውነገር የለም ፡ ከስራ ሲማለስ ቤቱ ውስጥንግስቱን ሲያገኝ ፣ ሲላፋት ፣ ሲታገላት አምሜጣአልጋውላይ ስትወጣና አማላጥኩህ አይነት አልጋውላይ ወጥታ በደስታ ስትጨፍር አሰታውሶ በደስታ ሊጦሙቅ ሲል በባህሪዋ መቀየር ምክንያት የተፈጠረውየ ቤቱ ጭል ማማጥቶ የትውስታውን ጥፍጥና አበረደው ፡ ከትካዜውሲወጣ ዩስራ ‹‹እሺ አንተኛውስ ስንት ትቆርጣለህ?›› አለችው ፡ ሰሚር ፈገግ ለማለት እየሞከረ ‹‹ሁለት ቁረጪልኝ!›› አላት፡ ፡ ዩስራ የልቧ ሰሚ ማሰል በአንዴ ስድስት ትኬት ሸጣእየተፍነ ከነ ከች ወደ ክፍሏ ገባች፡ ፡ እንደለሜደችውየ ኢስማኢልን ነሺዳ ልታደምጥ!
.
ዩስራ የአስራሁለተኛ ክፍል የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ከወሰደች ሁለት ሳምንት ቢሆን ነው ፡ ከውብቷምውዲያ ከተጨዋችነቷምበላይ ተነ ጥላ የምትታወቀውበነሺዳ አፍቃሪነቷ ነው ፡ የነሺዳ ሜድረክ ከተዘጋጀ የማነምይሁን የማነ ትኬት ከማሻጥ ጀምሮ በእለቱ እስከማስተባበር ድረስ በየቦታውእርሷ አለች፡ ፡ አሁንምበቅርቡ የሜሚ ቀውን የኢስማኢልን አዲሱን ነሺዳ እያዳማጠች ስለኢስማኢል ታስባለች፡ ፡ ኢስማኢል አጠር ያለ እጅጉን ውብ ድምፅ ያለውሙ ሺድነው ፡ ከዩስራ ጋር በጣምከመቀራረባቸውየ ተነ ሳ ነሺዳውን ከሜለቀቁ በፊት ሙሉውን አዳምጣአስተያየት እንድትሰጠውበሲዲ ሰጥቷታል፡ ፡ መቀራረባቸውግን ከተራውመቀራረብ ትንሽ ለየት እያለ ሳይመጣ አልቀረም ፡ ረዥምሰዓት በስልክ ሜውራት አንዳንዴምበአካል እየተገናኙ ሻይ ቡና ማለት ጀምሪዋል፡ ፡
..
...
....
ክፍል ሁለት (2) ይቀጥላል …

ግርዶ

ክፍል ሁለት (2)
(ፉአድ ሙና)
.
ዘቢባ የዩስራን ሜኝታ ቤት በር አንኳኳች። ምላሽ ሳትጠብቅ በሩን ከፍታውገ ባችና ጆሮዋ ላይ የጆሮ ማዳመጫየ ሰካችውን ዩስራን እያየች ‹‹እሺ ቀዌ የዛን የፈረደበት ልጅ ጩኸት እያዳመጥሽ ነ ው?››
አለች፡ ፡ ዩስራ ፈገግ

እንደማለት ብላ ዝምአለች፡ ፡ ዘቢባ የዩስራን የጆሮ ማዳመጫበጣቶቿ አወለቀችና ‹‹አንቺ አዝግ ይብቃሽ እስኪ እኛንምአዳምጪን!›› አለች፡ ፡
‹‹ምን ድነ ውልስ ማበ ታ ምን ልታወሪኝ ነ ው?››
‹‹ባክሽ እነ ሪቾ ቤት ዛሬ ምሳ አለ፡ ፡ ፀጉር ቤት ልሄድ ነ በር ከያፊ ጋር የሆነ ቦታ ደርሰን ልንማጣ ስለሆነ አልደርስም ፡ ዝምብለሽ በሶስት ስሪኝ!››
ዩስራ ከተቀማጠችበት ወንበር ተነ ስታ አልጋውላይ ተቀማጠችና ወንበሩን እግሮቿ ሚህል እያማቻቸች እንድትቀማጥ ጠቆማቻት፡ ፡ የዘቢባ ረዠምፀጉር ከወገ ቧ ላይ ሲነ ሰነ ስ የዘቢባ አይን ከፀጉሮቿ ማካከል ነ ጭወደሆኑ ት ሁለቱ አረፈ፡ ፡ ሁለቱ ሽበቶች አስራሁለት አመት የኋሊት ይዘ ዋት ሽማጡ፡
የዛሬ አስራሁለት አመት የአስር አመት ህፃ ን እያለች ነ ው፡ ከትምህርት ቤት ሜልስ ዩሱፍ እጇን ይዟት ወደ ቁርዓን ቤት ያማራሉ፡ ፡ የሶስት አመት ታላቋ ነ ውና እንደታላቅነ ቱ ይንከባከባት ነ በር፡ ፡ ከሜድረሳውግቢ ሲደርሱ ሜድረሳውከአሊፍ ክፍል ተማሪዎች በሚወጣውውብ ድምፅ ተውቧል፡ ፡ ‹‹አሊፍ ፈታአ ፣ አሊፍ ኪስራኢ፣ አሊፍ ዱማኡ አኢኡ ፤ ባ ፈታባ ፣ ባ ኪስራቢ፣ ባ ዱማ ቡ ባቢቡ ....›› እያሉ እጅግ ባሚ ዜማይዘ ምራሉ፡ ፡ ዩሱፍ ዘቢባን ወደ መሚያ ክፍሏ አድርሶ እሱ ወደ ክፍሉ ሄደ፡ ፡
ዘቢባ የምትማርበት ክፍል ᎓ ክፍል ይባላል። ቁርዓን ማንበብየ ቻሉ ተማሪዎች የሚማሩበት ክፍል ነ ው። ዩሱፍ ደግሞከሷ ክፍል አንድ ደረጃ ከፍ በሚ.ውልቲ ክፍል የቁርዓን ሽምደዳ እና የሀዲስ ትምህርቶች ይማራል። ዩሱፍ ወደ መሚያ ክፍሉ ሄዶ ትንሽ ከቆየ በኋላ የዘቢባ ጓደኛ ሀሊማ አስጠራችው። ሲወጣሀሊማእያለቀሰች «ያፊ ያፊ አብዱልከሪምየዘቦን ሂጃብአወለቀባት።
እያለቀሰች ነ ው።" አለችው። ዩሱፍ በእጁየያዘውን ኪታብ ጥሎሲከንፍ ወደ ዘቢባ ክፍል ሄደ።
ኡስታዙ ከበውት ቁርዓን በሚያሰሙህፃናት ተከልሏል። ዘቢባ በግራ በኩል በሴቶች ረድፍ ተቀምጣ ታለቅሳለች።
ከአጠገ ቧ እየተንበረከከ "ዘቡ ማ ውን? ንገ ሪኝ ማ ውን?" አላት። ሰውነ ቱ በቁጣይርገ ፈገ ፋል።
እንባዋን በሂጃቧ እየ ጠረገ ች "በህፃ ንነ ቷ አሮጊት ረግመዋታል ፣ ፀጉሯ ነ ጭነ ውብሎሂጃቤን ፈታብኝ!" ሳግ አቋረጣትና ቀጥላ "አብዱልከሪም" አለች። ዩሱፍ ከሂጃቧ ላይ የሂጃብ ማስያዣውን ሞርፎ ነ ቅሎ ወደ አብዱልከሪምተንደረደረ። ክፍሉ በጩኸት ሲታማስ ዩሱፍ ሲሮጥ ወደመሚያ ክፍሉ ተማለሰ። ኡስታዙ የ ጩኸቱን ምክንያት ሲያጣራ የአብዱልከሪምእጅ በሂጃብ ማስያዣ ተወግቶ ተገ ኘ።
በእርግጥ ድንጋጤውጣራውእስኪነ ሳ አስጮኸውእንጂ አብዱልከሪምብዙምአልተጎ ዳምነ በር። ከዛች ቅፅበት በኋላ አንድምቀን ዘቢባን በክፉ ተተናኩሏት የ ሚያውቅ የ ለም።
ሰራተኛቸው"ዘቦ እቴቴ እየ ጠሩሽ ነ ው" ስትል ከሰመመኗ ነ ቃች። ዩስራ በግርምት እያየ ቻት ነ በር።
"ስሚየ ት ሄደሽ ነ ው? ሰርቼሽ ከጨረስኩሽ እኮ ቆየ ሁ!" አለች።
ዘቢባ እንደሚደንገ ጥእያለች "ኧረ የ ትምአልሄድኩም" አለችና ወደተጠራችበት ክፍል ለሜሄድ ተነ ሳች። በውስጧያውየ ፈረደበት አግቢ የ ሜል ንዝንዝ እንዳይሆን ፈጣሪዋን ለማ ነች።
*
ሰሚር ወደ ቤቱ ሲማለስ ኸሉድ ቤቱን አፀዳድታ ጨርሳለች። ቁርስ አቀራርባ እንደፎከረችውምአኩርፋ እየ ጠበቀችውነ በር። በሩን አንኳኩቶ ሲገ ባ ሳትፈልገ ውኩርፊያዋ ሁሉ ከዳት። ፈገ ግ አለች።
ሰሚርን አተኩራ አየ ችውና እየ ተራመደች ተጠጋችው። አይኗን ትከሻውላይ ተክላ በደንብ ከተማለከተችውበኋላ ለስለስ ባለድምፅ "የኔ ቆንጆ በዚህ ጠዋት በሽሚዝ ይወጣል? በደንብ ሳይነ ጋ እኮ ነ ውየ ወጣኸው። ቢያንስ ጃኬት ነ ገ ር አይደረ ብም?" አለችው።
ሰሚር ቅድምእንዲያ ሲያበሳጨውየ ነ በረውንግግሯ በዚህ ሜልኩ ሲቀየ ርበት እና ጠዋት ምን እንዳለችውእንኳ እንደማታስታውስ ሲማለከት ግራ ተጋባ። ፈገ ግ ለማለት እየ ሞከረ "ጠዋት ስወጣ ያልሽኝን ታስታውሻለሽ?" አላት።

ግንቧሯን ቋጠር እንደሚድረግ አለችና እየለቀቀችው"እንዴ ሰሜ አንተ ስትወጣእኮ እኔ ተኝቼ ነበር። " አለችው፡፡ ሰሚ ጉዳዩን ማክረር ስላልፈለገ በልቡ"እንኳንምያላስታወስሽ" እያለ አቀፋትና ወደ ሚጅሊሱ ሄደውተቀማጡ፡፡ ልቡ የፀባይዋ መቀያየር ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚቻል ይገምታል። የቀዳችለትን ሻይ እየጠጣ ቅድምዩሱፍ የጠየቀውጥያቄ ትዝ አለውና ጠየቃት። በግራ ክንዱ እንዳቀፋት ጉንጯን ሳማና "ስሚኝ ማኹሉዴ፤ የወር አበባሽ በዚህ ሳምንት ማምጣት ነበረበት አይደል? እንዴት አልመጣም?"

አላት።
የቀኝ ጉንጯስርጉድ ጉንጯን ሁሉ ሞልቶት እስኪሰረጉድ ድረስ እየሳቀች "ይህቺ ጡጋ ጡጋ ፈለግሽ እንዴ?" አለችው፡፡
እየሳቀ "እንደሱ ሳይሆን አረገዝሽ ወይ ማለቴ ነው፡፡ " ብሎ የጉንጯ ስርጉድ ሳመው፡፡
የፈገግታዋ ውብት እንዳበበ "ልክ ነህ የወርአበባዬ አልመጣምግን አንዳንዴ እንደዚህ የቀናት ምናምን ለውጥ ሊኖረውይችላል። ስለዚህ አርግዤ ይሁን አይሁን ማውቅ አልችልም፡ " አለችው፡፡
በእርግጥ ለመውለድ ስለተስማሙምንምአይነት የእርግዝና መከላከያ እየተጠቀሙአይደለም፡
ፀባይዋ ግራ ቢገባውምግር እንዳለውላለማስታወቅ እየሞከረ "በቃ ይሄን ወር እንየውና ከሌለ ምርመራ ታደርጊያለሽ!" አላት።
ቁርሳቸውን በልተውሲጨርሱ እሁዳቸውን የሚያሳልፉበትን እቅድ ማደፍ ጀመሩ።
*
ዩሱፍ የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ነው፡፡ አባቱ በሞት ከተለዩ በኋላ ቤተሰብ የማስተዳደር ሀላፊነት የወደቀውእርሱ ላይ ነው፡፡ መርካቶ ላይ ካሏቸውሱቆች በተጨማሪ አንድ የሚያከራዩት አፓርትመንት ሳርቤት አካባቢ አላቸው፡፡ ዘቢባ የዩሱፍ የአጎት ልጅ ናት። ያለማታደል ሆኖ የእርሱምየእርሷም ወንድማማች አባቶች ህይወት አልፏል። የዘቢባ እናት አሜካ ናቸው፡፡ ልውሰድሽ ቢሏት አሻፈረኝ አለች። ከህፃንነቷ ያደገችበትን ቤት ለቆ መሄድ የሞት ያህል ይከብዳታል። ከእናት ፍቅር የበለጠበት ምክንያት ግን ግራ ነው፡፡
ዛሬ ዘቢባ እና ዩሱፍ መካኒሳ አካባቢ ከሚገኘውቤታቸውራቅ ብሎወደሚገኝ አንድ ወላጅ ያጡህፃናት ማሳደጊያ ለሜድ አቅደዋል።
ዩሱፍ በበሩ አንገቱን አሾልኮ ዘቢባን እያየ "እሺ እንውጣ!" አለ። ዘቢባ ከዩሱፍ እናት ወ/ሮ ጀሚላ ጋር ተቀምጣእያወራች ነበር።
ዩሱፍ መኪናውን ከግቢውአውጥቶ የመኪናውን ጡሩምባ ሲነፋ ዩስራ ከዘቢባ ጋር ተከትላ መጣች።
"እሺ ሰዎች ወዴት ናችሁ?" አለች በፈገግታ እየታጀበች። "የቲምሴንተር እየሄድን ነውከፈለግሽ ተቀላቀይን!" አለ ዩሱፍ። ከልቡ ግን አልነበረም፡ ዘቢባ የጋቢናውን በር ከፍታ ገባች። ዘቢባ እርሳስ ማቀለምያለውሙሉ ቀሚስ ለብሳ አምሮባታል። ከላዩ ጥቁር ኮት ደርባለች። ዩሱፍ ጥቁር ሰሚያዊ ኮት በጥቁር ጅንስ ሱሪ ነውየለበሰው፡፡ ዩስራ እየሳቀች "እንዲህ ሽክ ብላችሁ የቲም ሴንተር? በሉ በሉ ተግባብተናል ይመቻችሁ። ባይሆን ስትመለሱ የሚጣፍጥ ቸኮሌት ካለ ይዛችሁልኝ ኑ!" ስትል ነቆራውን ብቷቸውሁለቱምሳቁ። ዘቢባ ቸኮሌት ስለምትወድ ከወጡሳይጋብዛት እንደማይመለሱ እርግጠኛ ነበረች።

.
ክፍል ሶስት(3) ይቀጥላል

ግርዶ
ክፍል ሶስት

(ፉአድ ሙና)
.
መኪናዋ ወደ የቲምሴንተር ማኸከርከሯን ከጀመረች በኋላ ዩሱፍ ዘቢባን ሰረቅ አድርጎ አያትና "ከእቴቴ ጋር ምንድን ነበር የምታወሩት?" ሲል ጠየቃት።
ፊቷ ላይ የመከፋት ድባብ እየተሳለ "ባክህ አግቢ ነውየምትለው፡፡ የሀጀር ወንድምኢድሪስ በእናቱ በኩል እቴቴን አናግሯት ነበር። እና ምን ታስቢያለሽ እያለችኝ ነው፡፡ በአሁኑ ግን የምትፋታኝ

አትማስልምበጣምአምረራለች። " አለችው፡፡
ዩሱፍ ፈገግ ለማለት ሞከረና " ይሄ ስድስተኛ ሰውሚሆኑ እኮ ነው፡፡ " አለ።
ጀነን እያለች "አዎ ስድስት መቶኛምቢሆን ግን እኔ አላገባም" አለችው፡፡

ሳቅ አለና "እና ለእቴቴ እንደዛ አልሻት?" ብሎ ጠየቃት።
አንገቷን ወደርሱ ዞር አድርጋ ገርመምአደረገችውና "ኧረ አላልኳትም፡ እያረሳሳሁ ሰበብ ደርድሬ እንደሚልፈልግ አስረዳታለሁ። " አለችና ሙሉ ለሙሉ ሰውነቷን ወደ ዩሱፍ አዙራ እየተቀማጠች "አንተ ምን ታስባለህ?" አለችው፡፡
"እኔ ማ.... " በረዥሙእንደመተንፈስ እያለ "እኔ ማምን አስባለሁ? ምንም" አለ።
ዘቢባ እንደመቆጣት እያለች "እንዴት ነውምንምየ ማታስበው!? በየቀኑ ከእቴቴ ጋር ሚ ታረክ እየሰለቸኝ ነው፡ በቃ ማፃፈጥ ያለብንን ያክል እንጋፈጥ! እስከሙቹ ነውድብብቆሹ። " አለች።
ዩሱፍ ሚኪናውን ጥግ አስይዞ አቆሞና ወደ ዘቢባ ሰውነቱን አዙሮ እየተደላደለ ጠንከር ባለ ድምፅ "ቀላል ይማስልሻል? እቴቴን በቀላሉ ማሳመን የምንችል ይማስልሻል? እንደዚህ ቀላል ነውእንዴ? እንደውይሄን ብንነግራት እትዬ አይናችንን እንኳ ለሞዋት ትፈቅዳለች?" አላት።
ዘቢባ እንባዋ እየቀደማት "እንዴታዲያ እኔ ሌላ ሰውላግባ? ከሚልወደውሰውጋር ልኑር? አትወደኝምእንዴ? ለምን ማፃፈጥ ትፈራለህ?" እንባዋ ጠይሙን ፊቷን አራሰው፡ ስታለቅስ አሳዘነችው፡ "ብወድሽማነውእንዲህ አጣበቂኝ ውስጥየወደቅኩት። ግን እቴቴን ለማሳመን ጊዜ ይወስዳል። አላውቅምብቻ!" ብሎ ሚኪናውን ሲያስነሳ "ግን ቢያንስ መንገዱን እንጀምር። ምንም ሳናደርግ፣ ምንምሳንሞክር አንሸነፍ!?" አለችው፡ ልሟዋ አንጀት ይበላል። ወደየቲምሴንተር የሚወስደውን መንገድትቶ ሚኪናውን ወደ ጎልፍ ክለብነዳው፡ በዚህ ስሜት ወደ የቲምሴንተር ሜዱን አልወደደውም፡
*
ዩስራ ክፍሏ ውስጥሆና ላፕቶፗን ከስፒከር ጋር አገናኝታየኢስማኢልን ነሺዳ እያዳማጠች ፀጉሯን ትፈታለች። ቀጭን ውብድምፅ ከስፒከሩ ይንቆረቆራል።
"መንገድ ጠፉን ፣ ሳትን መንገድ፣
ከእውነት ጋር የሚጣጣም፣ የሚዋደድ።
እዝነትህ ላይ ተንጠልጥለን ፣ ያንተን ቁጣዘንግተናል፣
ወንጀል ሰርተን አይከፋንም፣ እንላለን ይምሯናል።
መንገድ ጠፉን ፣ ሳትን መንገድ፣
ፍርሀት አዝሎ፣ አንተን 'ሚወድ።
ፊትህ መቆም፣ እንዴት ሆኖ ይታሰባል፣
ሚውራት ላንችል ፣ ወንጀል በዝቶ አፍኖናል።
መንገድ ጠፉን ፣ ሳትን መንገድ፣
ከእውነት ጋር የሚጣጣም፣ የሚዋደድ። " የሚሉት ስንኞች በኢስማኢል ድምፅ ተኩለውከስፒከሩ ይፈሳሉ። ዩስራ ፀጉሯን አበጥራ ስትጨርስ ነሺዳውን አጠፉችና ስልኳን አንስታ ኢስማኢል ጋር ደወለች። ስልኩ እንደተነሳ በሳቅ በታጀበ ድምፅ "እሺ ሰውየው" አለች። ለሳቋ ምላሽ ይሆን ዘንድ በሷ ድምፅ ትይዩ በሳቅ በታጀበ ድምፅ "እሺ ዩሳዬ" አለ።
ስለ አዲሱ ነሺዳውአንዳንድ አስተያየቶች ከሰጠችውበኋላ ረቡዕ ለማ ናኘት ተቀጣጥረውስልኩ ተዘጋ። ስልኳን አስቀምጣ ወደ ሳሎን ስትሄድ አጎቷን ሳሎን ውስጥ ቆሞሲንጎራደድ አገኘችው፡ ይሄ አጎቷ የእናቷ ወንድምነው፡፡
ማማጣቷን ሲማለከት ከመንጎራደዱ እየተገታ "ዩስራ ትንሿ! እንዴት ነሽ? እነ ዩሱፊስ?" ብሎ ጥያቄውን አዥጎ ደጎደባት።
ስለምትወደውዘላ ጉንጬን ሳመችውና "አለሁልህ ከሚሌ! ዘቢባ እና ዩሱፍ የቲምሴንተር ሄደዋል። ተቀመጥ። " አለችውበእጇ አረቢያን መጅሊሱን እየጠቆመችው፡ ሳቅ አለና "ሀላል መዝናኛ ሚሆኑ ነው?" ብሎ ተንከትክቶ ሳቀ።
በግርምት እያየችው"ምንድነውየ ሚያስቅህ?" አለችው፡ ከሳቁ እንደሚ ታት አለና "የቲም ሚ ብኘትማቆንጆ ነገር ነበር። ግን የአሁን ጊዜ ልጆች የቲምአጡያየ ቃችሁ ውል አልባ ነው፡ ግር

ብላችሁ ትሄዱና ተዝናንታችሁ ምናልባትምከልጆቹ ጋር ሳታውሩ ከተታችሁን ጥላችሁላቸው ትመጣላችሁ። የእንስሳ ፓርክ እንደሚ በኝ ሰውእያያችኋቸው'ያቺ አታምርም? ያቺኛዋን እያትማ ተባብላችሁነውየ ምትመጡት። የእውነት ድጋፍ

እንደሚያስፈልጋቸውአስባችሁ ልትንከባከቧቸውሳይሆን የአንድ ሰሞን ፋሽን ሆኖባችሁነው። ለሰልፊ ማስሚያነትነውየ ምትጠቀሟቸው። " አላት።
ዩስራ ከት ብላ ሳቀችና "እኔ አዎ እንደዛ ነኝ ግን ያፊ እና ዘቦ እኮ በወር አንዴ ምናምን በቋሚነትነውየ ሚሄዱት። " አለችው።
ወደ ኮሪደሩ እየተመለከተ "በይ ይሁንልሽ። መኝታ ቤት ግቢና እናትሽን እንደመጣሁ ንገሪያት። " አለ። ልትጠራለት ወደ መኝታ ቤት ሄደች።
*
.
ክፍል አራት (4) ይቀጥላል

ግርዶ

ክፍል አራት

.
ዘቢባ እና ዩሱፍ ወደ ቤት ሲመለሱ ለዩስራ ቴክ አዌይ ፒዛ እና ከእነሱ የተረፈ ቸኮሌት ይዘውመጡ። ልክ በር ጋ ደርሰውየ ሚኪናውጥሩምባ ሲሰማዩስራ ከሰራተኛቸውቀድማእየ ሮጠች በሩን ከፈተች። ሚኪናውውስጥ ዘቢባ ሞሯ ግራ እያጋባት "እንዴሪቾ ጋር አብራችሁ ሄዳችሁነው? እንዴት አብራችሁ መጣችሁ?" አለች። ዘቢባ ከሚኪናውወርዳ ቸኮሌቱን እና ፒዛውን እየሰጠቻት "አብረን ገባ ብለን ወጣን። ስለደበረኝ መቆየት አልፈለግኩም፡ " አለች።
ዩስራ በሀዘን አይን አየ ቻትና "ውይ እነሱ ደሞተዘጋጅተውልሻል። ዛሬ አይፈቱሽም!" አለችና እየተንደረደረች ወደ ቤት ገባች። ዩሱፍ ሚኪናውን አስተካክሎበሩን ዘጋና ወደ ዘቢባ እያየ "በይ ረጋ ብለሽ አውሪያቸውእንዳታስፎግሪ። " አላት። ንግግሩ አልጣማትም፡ እንዳኮረፈች ትታውወደ ቤት ገባች። የሷ ፍላጎት ዛሬ እውነቱን ፍርጥርጥ አድርጎ መናገር ነበር። የሱፍ ከኋላዋ ቆሞበእርጋታ አያት። ሚልካምነቷ፣ በጠይምፊቷ ላይ የሚቁለጨለጩ ትላልቅ አይኖቿ፣ ስትስቅ የሚሸበሸበው አፍንጫዋ፣ ሁሉ ነገሯ ለእርሱ ውብነው። ዳሌዋ በማጡኑ ወደ ወገቧ ጥብብ ይላል። ከህፃንነቱ ጀምሮ ተላምዷታል። ጨክኖ የእናቱን በባህል የተሸበበ እምነት ማክበር የከበደውምለዚህ ነው።
ወደ ቤት ሲገቡ የዩሱፍ አጎትና እናት አረቢያን መጅሊሱ ላይ ተቀምጠውቡና እየጠጡነበር። ቤቱ በእጣን ጭስ ተጣጥኗል። ዘቢባ ሰላምብላቸውልብሷን ልትቀይር ወደ መኝታ ክፍሏ ልትሄድ ስትል ወ/ሮ ጀሚላ "እስኪ ዘቦ ነይ እዚህ አጠገቤ ቁጭበይ!" አሏትና ከተቀመጡበት በቀኝ በኩል መጅሊሱን በእጃቸውቸብ ቸብ አደረጉላት። የፈራችውእንደደረሰ ገብቷት ልቧ እየ ፈራ ቁጭአለች። ዩሱፍ ስለ ጋብቻ ሊያወሩ እንደሆነ ስለገባውተነስቶ ወደ ክፍሉ ሄደ።
"እሺ አበባዬ" አሉ ወ/ሮ ጀሚላ የቡናውን ሲኒ ወደ ግራ ተለጥጠውለሰራተኛቸውእያቀበሉ። ቀና አሉና ንግግራቸውን ቀጠሉ "ዛሬ ይኸውከሜሌምአለ በጋብቻውዙሪያ ምን እንዳሰብሽ ትነግሪናለሽ! ዛሬ ምንምሰበብ አልፈልግም፡ ኢድሪስ ያውእንደምታውቂውጥሩ ልጅነው። ሀይማኖቱን አክባሪነቱ ብትይ ወላ ስነ ምግባሩ ምንምአያንሰውም፡ እድሜውምከዩሱፌ ብዙምአይለይም፡ እሱ በሰኔ ተወለደ ዩሱፍ ደግሞሁለት ወር ዘግይቶ ማስከረምላይ ተወለደ። ስለዚህ እኔ የሚጅሽ ይማስለኛል። ቤተሰቦቹም ስርዓት ያላቸውናቸው። አሁን የቀረውያንቺ ውሳኔነው። አንቺ ምን ትያለሽ?" አሉና ወደ ከሜል ዞር ብለው"ከሜሌ የምትለውነገር ካለ በላት!" አሉ። አቶ ከሜል በከፊል የነጣፂሙ በጣቶቹ አሻሽ ጡና "ያውእንደምታውቂውየ ሴት እድሜከሄደ ሄደነው። ይሄ ሰውስድስተኛ ጠያቂነው። ግን እሱንም አልፈልግምማለት መብትሽነው። ታዲያ በቂ ምክንያት ግን ሊኖርሽ ይገባል። የዘንድሮ ልጆች በጊዜ ልቤን ለልብህ የማባል አባዜ አለባችሁ። እንዲያምከሆነ ወዲህ በይውና እንምከርበት። " አለ።
ወ/ሮ ጀሚላ ቀበል አደረጉና "እህሳ ያንቺ ሀሳብ ምንድነው?" አሉ። ዘቢባ እጆቿን ከጭኖቿ ስር እያፋተገች ዝምብላ ከቆየች በኋላ "እቴቴ እኔ ማግባት አልፈልግም!" አለች። "እኮ ምክንያት!?" ቁጣቸውከገፅቸውይነበባል።

አንገቷን ሰበር እንዳደረገች "እኔ የምወደውን ሰውነ ውማገባት የሚፈልገው።" አለች። አቶ ከሚል አተኩሮ ተመለከታትና "ቢያንስ ቀርበሽውእንኳ ለማየት እኮ ፈቃደኛ እየሆንሽ አይደለም፡ እንዲሁ ገና ከጅምሩ እንቢ የምትይውቆይ አንቺ ማግባት የምትፈልጊውሰውአለ እንዴ?" አላት። ወ/ሮ ጀሚላ ቀበል አድርገው"በያ በይ ሜላሽለት!" አሉ። ዝምስትል ወ/ሮ ጀሚላ በቁጣድምፅ "ከንዚያ ቀን ማታ እየደወለች ልጄን ካልዳርሽ ትለኛለች። እሷ እኔ ችላ ያልኩሽ ነውየሚሞትላት። በዚህ በኩል አንቺ አልነ ካምትያለሽ። በሚህል ቤት እኔ እጠበሳለሁ። ቆይ ምንድነ ውሀሳብሽ?" አሉና ወደ ሰራተኛቸው ዞር ብለው"ሂጂ እስኪ ዩሱፌን ጥሪልኝ!" አሉ።
ዩሱፍ ወደ ሳሎን ብቅ ሲል እናቱ "ትሰማኛለህ ዩሱፌ! የዚህች ልጅ ችግር ሊገባኝ አልቻለም፡ አንተን ትሰማህለችና የምትመክራት ከሆነ ምከራት። ነገ ማግባት የምትፈልገውን ሰውእንድታሳውቀኝ እፈልጋለሁ። ምከራት በእድሜዋ አትጫወት!" አሉት። ፈገግ ለማለት እየሞከረ "እረ እኔ አወራታለሁ ችግር የለምነገ ታሳውቃችኋለች።" አለ። ዘቢባ ቀና ብላ አየችውና ፈገግ አለች።

.

የሱፍ የዛን ቀን ማታ በቅጡአልተኛም፡ ደፍሮ ለእናቱ ዘቢባን ላግባት ቢል ሊከተሉት የሚችሉትን ምላሾች እያሰበ ለሊቱን እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር አደረ። "ምናልባት እኮ እቴቴምደስ ሊላት ይችላል!" ብሎቅዠት የሆነ ተስፋ ለራሱ ይሰጥና ፍፁምእንደማይሆን ሲያስብ እንባ እንባ ይለዋል። ያኔ ድሮ በነፃነት ይቦርቁ የነበረበት ጊዜ ይናፍቀውና በትዝታ ወደዚያ ሜላካምጊዜ ይነጉዳል። ያኔ የዘቢባ አለምእሱ ብቻ ነበር። የእርሱምአለምዘቢባ ብቻ ነበረች። ሁሌምቁርዓን ለመቅራት ወደ መድረሳ የሚሄዱት ወይ አቅፏት አሊያምእጇን ይዟት ነበር። ታዲያ የዘቢባ እድሜአስራአምስት ከሞላ በኋላምተያይዘ ውምሆነ ተቃቅፈውሜዳቸውን አልተውምነበር። መድረሳ ውስጥ ኡስታዞቹ ወንድምና እህት ስለሚመስሏቸውእንደውምለሌላውተማሪ የእህት እና የወንድምፍቅር ማስተማሪያ ያደርጓቸውነበር። ኋላ ላይ ግን የወንድማማች ልጆች መሆናቸውሲታወቅ የመድረሳውርዕሰ መምህር ቢሮ አስጠርቶ ከዚህ በኋላ ማ ካካትምሆነ ለብቻቸውአብረውመሆን እንደሌለባቸውይነ ግራቸዋል። እነርሱምየአጎት ልጅ መነካትምሆነ ያለ ግርዶ አብሮ መሆን እንደማይቻል በደንብ ኪታብላይ ቀርተውታል። ግን ስለነሱ እንደሆነ አስበውትምአያውቁም፡ ብዙዎች መፅሀፍ ላይ ያሉ ነገሮች ስለመፅሀፉ እንጂ ስለእኛ አይመስሉንም፡ ዩሱፍ ዘቢባ ርዕሰ መምህሩን እያየች "ለምንድነ ውየማንነካካው?" ስትለውኡስታዙ ግራ እየገባው"አንቺ ኪታብአይደል እንዴየምትቀሪው? ይሄን አታውቂም? ማግባት የሚያስችል ዝምድና ነውያላችሁ! ስለዚህ ማ ካካት አትችሉም!" ሲላት ፈገግ ብላ "ውይ እንደሱከሆነ ማበቃእንጋባለን!" ያለችበት ቀን ትዝ አለውና ብቻውን ሳቀ። የዛን ቀን ኡስታዙ እየቀለደችበት መስሎት እጇ ፍምእስኪመስል ሲገርፋት ያመመውዩሱፍን ነበር። ዘቢባ ስታለቅስ ዩሱፍ አቅፎ ሲያባብላት ኡስታዙ አይቶ የልጆቹ ፍቅር የእውነት እንደሆነ ገባውና "አይ እናንተስ እውነ ትምተጋቡ!" ብሎትቷቸውሄደ። ኋላ ላይ ግን የሚያደርጉት ነገር ለተማሪውመጥፎ አርዓያ እየሆነ እንደሆነ ሲሰማቸውዩሱፍ ኪታብምብዙ ስለቀራ አስራ ስምንት አመትምስለሞላውሌላ ቦታ ይማር ብለውአባረሩት። ዘቢባ እና ዩስራ ብቻቸውን እዛ መድረሳ መማር ቀጠሉ። ሆኖምወደ መድረሳ ሲሄዱ ማሻኘትና ሲማሉበር ላይ ጠብቆ አብሮ ከመማለስ ዩሱፍን ያገደውነገር የለም፡ ለወ/ሮ ጀሚላ ሶስቱምእንደ ልጅ ስለነበሩ ይህን ቀረቤታቸውን አንድምቀን በሌላ አይን አይተውት አያውቁም፡ ከጣፋጩትዝታ ሲማለስ አሁን ላይ ያለበት አጣብቂኝ ይደብረውና ተሜሉሰ ወደ ትዝታውይጓዛል። ትዝታ ደግሞክፉ ነውአዙሮ አዙሮ ዛሬውላይ ይሜሉሰዋል። ድሮ በነፃነት ይተቃቀፉ ነበር። እድሜያቸው ከፍ ሲል ግን የሰውምግልምጫሲያስቸግራቸውበሰውፊት ተቃቅፎ ሜዱን ትተውታል። ግን ያላቸውን ጊዜ በሙሉ አንድ ላይ ነውየሚያሳልፉት። ነገ ለእነሱ ምናልባትምጥሩ ቀን ነው። እስከዛሬ የታፈነውን ድብቁን ፍቅራቸውን ይፋ ያወጡብታል። ምላሹ ግን መደሰትምመከፋትምሊያስከትል ይችላል። ግን በጣምፈርቷል። ከሷ ጋር ካልሆነ ምድር ላይ መኖር የሚችል አይመስለውም፡ ነገ ግን ቁርጡን ያውቃል።
*

ጠዋቱን ዘቢባ እና ዩሱፍ ቁርስ በልተውእንደጨረሱ ወደ ስራ ለሜድ ማላባበስ ጀመሩ። ለባብሰው ሲወጡውወ/ሮ ጀሚላ ከኋላ ተከተሏቸውና "ነግሬሀለሁ ዩሱፌ ዛሬ የሜጨሻዋ ነውበደንብአማክራትና ትወስን! አለበለዚያ ግን ማታ የኔን ውሳኔ አዘጋጅቼ እጠብቃታለሁ።" አሉ። ዘቢባ ሳቅ ለማለት

እየጣከረች ወደ ሚኪናውገቡና ወደ ሚካቶ ተሽከረከሩ። "እህ አማካሪውአማክረኛ!" አለችና ጮክ ብላ ሳቀች። ሳቁ እየተጋባበት "ምን ላማክርሽ? ቆይ ኢድሪስን ለምን አታገቢውም?" አለ። ኮስተር እንደማለት አለችና "አሁን በዚህ ሰዓት ይቀለዳል? ፕሊስ ዩሱፌ እንጋፈጥ!" አለችው። አይኑን ከመንገዱ ወደእርሷ እየመለሰ "ሌላ አማራጭአለን እንዴ?" ሲላት ደስታዋ አቅሏን አሳጣት። ጉንጩን ሳመችው፡ "ልንዳበታ ሴትዮ!" አለ ፊቱን ከእጇ እያስለቀቀ። ደስ ብሎታል። ስለሳመችውምብቻ ሳይሆን ደስ ስላላት ደስ ብሎታል። ሚካቶ ገብተውሁለቱምየገቡእቃዎችን ለማየት ወደ ማጋዘን ሄዱ።
የሁለቱምተስፋ ምናልባት አንድቀን ይህ ፍቅራችን የፈጣሪን ይሁንታ አግኝቶ ህጋዊ ይሆናል የሚል ነው።
*
ኸሉድ የባሏ ሳይሰናበታት መውጣት ግራ ገብቷታል። እንዳኮረፈች ደወለችለት። "ሁቢ" አለች ስልኩ ከማ ሳቱ። ሰሚር ምርር እያለው"ኧረ ተይ መቀለጃ አታድርጊኝ ተይ!" አለ። ሆዷን ባር ባር እያለው "ምን አጠፋሁ ደግሞ? ጠዋት በተኛሁበት ቻውእንኳ ሳትለኝ እኮ ነውየሄድከው! ደሞትቆጣለህ እንዴ!" እንባዋ ከአይኖቿ ፈሰሰ። ሰሚር ከባድየፀባይ ለውጥእንዳመጣአሰበች። "በቃ አሁን ቢሮ ነኝ ብዙ ፔሽንት አለብኝ። ስማለስ እናወራበታለን። ደህና ሁኝ!" ብሎስልኩን ዘጋው፡ "ጩሖሽ ስልክ ማዘጋት? እኔ ላይ?" አለች ስልኳ ላይ እያፈጠጠች። ሆድባሳት። ለሱ ብላ ፤ ቤቱ በሰራተኛ እንዳይፀዳ ፣ ሰራተኛ የሰራውን እንዳይበላ ስንት አመት የለፋችበትን የጤና ማካንንነት ዲግሪዋን ቁምሳጥኗ ውስጥእንዳልወረወረች ፤ ዛሬ እሷ ቤት ስትውል የሱ ፀባይ ሲቀየርባት ሆድባሳት። የጉንጯ ስርጉዶች እንባ እስኪያቁሩ ድረስ አነባች። "ሺ ወንድ ሲጋደልልኝ ፍቅሩን ብዬ ይሁንታዬን ብሰጠው፣ ሴትነቴን ባሳቅፈውስልክ እኔ ላይ? እኔ ላይ ይዘጋል?" ተንሰቀሰቀች። አንብታ ስትጨርስ ስልኳን አነሳችና አንድ ቁጥር ፈለገች። በቅርቡ አብራት የተማረችውጓደኛዋ እሷ የምትሰራበት ሆስፒታል የስራ ቅጥር ማስታወቂያ ማውጣቱን ነግራት ነበር። ያስናቃት ቤት መቀመጧእንደሆነ ተሰምቷታል።
"ወጣወጣስል እኔ ምምንምእንደማያንሰኝ ይረዳል!!" ልቧ ክብሯን ስለማስማለስ ያስባል።
የደወለችውስልክ ተነሳ። "እሺ ኸሉድ ሳቂታዋ" አለች ነዒራ ስልኩን አንስታ። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ "የባለፈውን ስራ እኮ አፕላይ ማድረግ ፈልጌ ..." አላስጨረሰቻትም"አላምንምኸሉድዬ በጣም ደስ ይላል በቃ ነገ ነውlast day of submission so ማስረጃዎችሽን ኢሜይል አድርጊልኝ እኔ አስገባልሻለሁ።" አለቻት። ነዒራ ኸሉድ ያን የማስለ ጩኸቅላቷን ይዛ ቤት መቀመጧእጅግ ያማት ነበር። ማስረጃዎቿን በኢሜይል ልትልክላት ተስማምተውስልኩ ተዘጋ።
"ያለነገርማእንዲህ አልሆነ ም! አንዷማልቡን አሸፍታዋለች!" አለች በልቧ። አንዳች ስሜት ውስጧን ተቆጣጠረው፡ ሂጃና ከኮንደሚኑየ መኮሪደር ላይ ዘለሽ ተፈጥፈጪ፣ ተፈጥፈጪአላት። ከቤቷ ወጥታ ከኮረደሩ ላይ ለመዝለል ስትሞክር ጎረቤቶቿ እየሩስአሌምእና ጴጥሮስ ያዟት። እንድትረጋጋ ቤታቸውአስገቧት። ከሰዐታት በኋላ ረጋ ስትል እየሩሳሌምን ቀና ብላ አየቻትና "ማ ውእዚህ ያመጣኝ?" አለች። ጴጥሮስ ፈገግ አለና "እንዴአሁን እትዬ ሽምኢያ አይተውባይነ ግሩን እኮ ዘለሽ ነበር። ቆይ ምን ሆነ ሽ ነው?" ኸሉድ ግራ እየተጋባች "የምን መዝለል ነው?" ያደረገችውን ከመጀመሪያውእስከመጨረሻ ነገሯት። "እኔ ለጓደኛዬ ስልክ ደውዬ እዚያ የሳሎን ቤት መጅሊስ ላይ ነበር የተቀመጥኩት! ከዛ የተኛሁነበር የማስለኝ።" እየሩሳሌምእስከአሁን ከድንጋጤዋ አልተላቀቀችም፡ "ሰሚር ጋር እንደውልለት!" ጴጥሮስ "አይሆንምይደነግጣል። ባይሆን ዛሬ አንቺም የትምስለማትሄጂ ጠብቂያትና ከስራ ሲመጣእንነግረዋለን።" አለ። ተስማምተውቀኑን ወደ ቤቷ ወስደውእየሩሳሌምስትጠብቃት ዋለች።

.

ክፍል አምስት (5) ይቀጥላል ...

ግርዶ

ክፍል አምስት

.

ከከሰዓት በኋላ ዩስራ መሻታ ክፍሏ ተቀምጣግጥምለማፍ እየጣከረች ሳለ ኢስማኢል ደወለላት።
"ሄሎ" አለች ስልኳን አንስታ።
"ዩስሪ ቆንጆ!"

"ቆንጆ?" ከዚህ በፊት ብሏት አያውቅም፡፡
"ምን ውትጠራጠሪያለሽ እንዴ?"
"አይ ማለቴ ትንሽ ግራ አጋባኸኝ" ድምጿ ተሰባበረባት። ዛሬ ደግሞ ከእንቅልፉ ስሜን ጠርቶ የተነሳ ይመስል ስለውበቷ ብዙ ዘባረቀ። ትንሽ ደስ ሳይላት አልቀረም፡ ወዶኛል ብላ አስባለች። በታዋቂ ሰው መወደድ ደስ ይላል።
ስለ ረቡዕ ቀጠሮቸውብዙ ካወሩ በኋላ "እወድሻለሁ። ባይ!" ብሎ ስልኩን ዘጋው፡፡ እወድሻለሁ
የእህትነቱ ነውወይስ ይሄ ፍቅረኞች የሚባባሉት? የእህትነቱ ከሆነ ለምን እስከዛሬ ሳይላት? "ይሄ ልጅ አፍቅሮኛል እንዴ?" ልቧ ጠየቀ። ስሜቷን ለሚረጋጋት እየሞከረች ወደ ግጥሟተመለሰች።
"ከዚህ ይታያል ፣ ባንተ ፍቅር የከበረ፣
በእንባ ሀይል ፣ ከጉንጬ ይ የፈጠረ።
ከቦዩ ላይ፣ ያለውፊደል
ለሚታገል ፣ የሚታደል፣
አለውታሪክ ፣ የሚደር የሚ ነገር።
ታሪክ 1
ነዳይ ነው፣ 'መቃምነውየሌለው፣
ሀብት አገኘ ፣ ለሱ ቢጤሌት አደለው፡፡
ደሀ ሆነ ፣ ካንተ ወዶ፣
አለምናቀ ፣ ያንተን ፍቅር ተዋህዶ።
ታሪክ 2
ሚስት ናት ፣ መጥፎ ባል አላት፣
የጎረቤት ፣ ወንድ ያስከጀላት።
ከሌላ ጋር ፣ ሲባልግ ባሏ፣
ያ ጎረምሳ ፣ ጠርቷት ክጅሏ።
ባሏን ሳይሆን ፣ አንተን ብላ፣
ተቃጠለች ፣ ስሜቱ አፍና።
ታሪክ ሲያልቅ
አለ እውነት ፣ ውብ ቁምነገር፣
ስሜቱ ክዶ ፣ ላንተ ሚደር።"
የፃፈችውን ግጥምአየችውና ደብተሯን ዘጋችው፡፡ የኢስሚኢልን የቀድሞነ ሺዳ ከፈተችና አልጋዋ ውስጥገባች። አየሩ ቀዝቃዛ ነው፡፡ እንቅልፍ ቀስ እያለ አሸለባት። ነሺዳውይጮኻል።
.
ወ/ሮ ጀሚላ የሜንታ ክፍሏን በር ሲያንኳኩ ዩስራ በህልሟየ ኢስሚኢልን አልበምምሪቃ እያየች ነበር። ሰውአንድ ላይ ሲጮህ እሷምበደስታ እየጮኸች ከእንቅልፏ ባነነች። የበሩን መንኳኳት ከህዝብ ጩኸት ጋር በገሚውአእምሮ እየተበሳጨች "ወዬ!" አለች። ወ/ሮ ጀሚላ በሩን ከፍተውአዩና "በይ ተነሽ! እነ ዘቢባ እየመጡነው! መሽቷል። ሰሚራ ስራ በዝቶባታል ጁስ ስሪ እስኪ!" አሉ። ሰሚራ ሰራተኛቸውናት። ወ/ሮ ጀሚላ እንደዛሬ በጉጉት የሚጠብቁት ምሽት ያለ አይመስልም፡ ዩስራ ተነስታ ጁስ እየሰራች የዩሱፍ ሚኪና ጥሩምባ ተሰማ፡ አስራ ሁለት ሰዓት ሆኗል። ዩሱፍ እና ዘቢባ ውስጣቸው ያለውን ጭንቀት ላለማሳወቅ ፊታቸውን የውትሮውን ገፅ ሊስሉበት ይታገላሉ። ዛሬ የጪ ቃቸው ላይመስሉ ይደክማሉ። ቤት ገብተውልብሳቸውን ከቀያየሩና መግሪብ ከተሰገደ በኋላ ሁለቱም ለነጋዴዎች ያስረከቡትን ሂሳብ ለሚጋገ ጥ ተቀመጡ። ወ/ሮ ጀሚላ እንደምንምጉጉታቸውን ውጠው ሂሳብ ሰርተውእስኪጨርሱ ከታገሱ በኋላ የመጅሊሱን ትራስ እያመቻቹ "እሺ አሁን እዚህ ጋ ኑ" አሉ።
የቁርጧሰዓት ደረሰች። ሳሎኑ ውስጥ ቡና የምታፈላዋን

ሰሚራን ጨምሮ ሁሉምአሉ። ዩስራ በጉጉት የዘቢባን አፍ ታያለች። ወ/ሮ ጀሚላ ቀጠሉ "ያውዛሬ ዩሱፌምእንዳማከረሽ እና ከውሳኔ እንደደረስሽ አስባለሁ። ስለዚህ ምን ወሰንሽ?" አሉ።
ዘቢባ እጆቿ መንቀጥቀጥጀምሯዋል። የለበሰችውሺቲ ንፋስ የሚያውለበልበውይመስል ይንቀሳቀሳል።
እንደምንምራሷን ለሚረጋጋት ሞከረች። ዩሱፍ ሊያበረታታት ፈገግ አለ። ፈገግታውትንሽ ድፍረት ሰጣት። ጎሮሮዋን ከጠረገች በኋላ "እሺ ያውእስከዛሬምየ ሚማጡትን ሰዎች ቀርቦ ለማየት ፈቃደኛ

የሚሆን ውየ ማስበውሰውስላለ ነው፡፡" አለች፡፡ ወ/ሮ ጀሚላ ፈገግ ለማለት እየሞከሩ "እ .... ሺ" አሉ፡፡ ዘቢባ ቀጠለችና "ስለዚህ ጋብቻውይቅርብኝ!" ስትል ወ/ሮ ጀሚላ ቀበል አድርገው"እኮ ማ ው? ንገሪንና የሚሆን ከሆነ ሰርጉ ይደረግ፡፡" አሉና ወደ ዩሱፍ እያዩ "አይደል እንዴ ዩሱፌ?" አሉ፡፡ የሱፍ በአዎንታ አንገቱን ነቀነቀላቸው፡፡ ዘቢባ ፍርሀቷ ጠናባት፡፡ እጆቿ አልታዘዝ አሏት፡፡ ዩሱፍ እንደምንምበፈገግታውሊያበረታታት ይሞክራል፡፡ ከፈገግታውውስጥየሚታያት አለሁልሽ የሚል ሚልዕክት አለ፡፡ የማጡውይምጣብላ የአሟታት ክንብንቡን መግፈፍ ጀሚረች፡፡ አንገቷን እንደሰበረች "እቴቴ እኔ ህይወቴን ሙሉ ስወደውየኖርኩት ሰውአለ፡፡ እርሱምበጣምይወደኛል፡፡ በስነ ምግባሩም ፍፁምየሚታች አይነት አይደለም፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ ስወደውሲወደኝ ነውየኖርኩት፡፡ እርሱበአንቺም ዘንድ ተወዳጅ ነው! እቴትዬ ያልተከለከለ ነገር ሁሉ የተፈቀደ ነው፡፡ እኛ በራሳችን ላይ ከፈጣሪ ያልተከለከልነውን ነገር እርምማድረግ የለብንም፡፡ የሰውልጅ መሙሪያ አምላካዊ ትዕዛዛት እንጂ ሰዋዊ አጥሮች ሊሆኑ አይገባም፡፡ እቴትዬ እናትነቱምአማችነቱምከአንቺ ውጪእንዲሆንብኝ አልፈልግም፡፡ ከያፊ ጋር እንፋቀራለን! ለኔ ከሱሌላ፣ ለእርሱምከኔ ሌላ ሚሻት የለም፡፡" አለች፡፡ ወ/ሮ ጀሚላ ድርቅ ብለውቀሩ፡፡ አይኖቻቸውሁለቱንምእያፈራረቁ ያያሉ፡፡ እንደእርሳቸውእሳቤ ምድር ሰማይ ልትባል ትችል ይሆናል፡፡ ሰማይምቀን ሲቀየር ምድር ቢባል ግድየለም፡፡ ግን ዘቢባ የዩሱፍ ሚስት ልትባል አትችልም፡፡ የወ/ሮ ጀሚላ አስተሳሰብ በፍፁምሊቀበለውየሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከድንዛዜያቸውሲሰክኑ፣ ከወደ ሙንቃቱ ሲጡጉ ወደ ዩሱፍ ዞር ብለው"የምትለውእውነት ነው?" አሉት፡፡ በዚህ ሰዓት አይደለምብሎየእናቱን ንዴት ቢያበርድ ደስ ባለውግን ዛሬ ሁሉምእውነት መፍረጥ አለበት፡፡ ራሱን አደፋፍሮ አይናቸውን እያየ "አዎን እቴቴ! ፍቃድሽ ቢሆንና በጊዜ ብንጋባ ደስ ይለኛል፡፡ ከሷ በላይ ማንምሊረዳኝ፣ እርሷንምከኔ በላይ ማንምሊያስብላት አይችልም፡፡ ደስታችን በእጅሽ ነውእቴቴ!" አለ፡፡ ዘቢባናዩሱፍ ልባቸውተሰቅሏል፡፡ ፊታቸውተሜፅኖ ለብሷል፡፡ ዩስራ ግን ያልጠበቀችውን ነገር አልሰማችም፡፡ ሁሌምበግልፅ ባታወጣውምትጠረጥረውየነበረ ጉዳይ ነው፡፡ ይፋ ሲወጣደስ አላት፡፡ ከልጅነት ቁርዓን ቤት ከሚሄዱበት ጊዜ ጀምሮ የፍቅራቸውምስክር ናት፡፡ ደፍራ ፍቅራቸውከወንድምና እህትነት የዘለለ ነውባትልምልቧ ግን በተለይ እድሜዋ ከፍ ካለ በኋላ በጣምይጠረጥር ነበር፡፡ ዩስራ ፀጥታውን ሰበረችው፡፡ "ወይኔ በአላህ ደስ ሲል! ኡሚገ ብቶሻል? ዘቦ እኮ የኛውልትሆን ነውማለት ነው፡፡" ስትል ወ/ሮ ጀሚላ ቀለብ አድርገው" ዝጊ አንቺ! ወረኛ! ነገ ደግሞአንቺምተነሽና የከሜኤን ልጅ አገባለሁ በይ! ባለጌዎች!" አሉ፡፡

"እቴ እኛ ስነ ስርዓት ይዘን ያደግነውበአንቺውእጅ ነው፡፡ እኔ እሷን ላግባ ማለቴ ብልግና ሊሆን የሚችልበት አንድምመሙዛኛ የለም፡፡ ለአንቺምለእኔ ውብትድሪያት ነውእረፍት የምታገኚው፡፡" ዩሱፍ ለማሳመን ይሞክራል፡፡

ወ/ሮ ጀሚላ ያፈኑት ቁጣቸውእየተንቀለቀለ ፊታቸውን ደምአለበሰው፡፡ " ትሰማላችሁ? ሁለታችሁ ወንድምእና እህት ናችሁ! በቃ ይኸውነው፡፡ ሌላ ዝምድና የላችሁም፡፡ ትንሿ ልጄን ለትልቁ ልጄ አልድርም፡፡ ሰውስ ምን ይለኛል? በፍፁም!" አሉና ከመቀመጫቸውተነስተው"እርሱት! ድጋሚ እንዳታነሱት! አንቺ ደግሞኢድሪስን ለማግባት ተዘጋጂ!" ብለውወደ መኝታ ክፍላቸውሄዱ፡፡ ዘቢባ እንባዋን መቆጣጠር አቃታት፡፡ ተንሰቀሰቀች፡፡ ዩሱፍ አቅፎ ያባብላታል፡፡ "አትሸነፊ! ሲነጋ እናወራታለን! ስትረጋጋ እሺ ትለናለች!" ይላታል፡፡ ዩስራ የዘቢባ እንባ ተጋብቶባት አብራ ታለቅሳለች፡፡ ትንሽ እንደቆዩ ዩሱፍ አባብሎሁለቱንምወደ መኝታ ክፍሎቻቸውወሰዳቸው፡፡ ሁለቱን አድርሶ ወደራሱ ክፍል ሄደ፡፡ እራት አለመብላታቸውን ማንምአላስታወሰም፡፡ ምናልባት ሰሚራም አላስታወሰችም፡፡ ሁሉምከአልጋቸውቢጋደሙምከሰሚራ

ሌላእንቅልፍ የወሰደውአልነበረም፡፡

*

ሰሚር ከስራ ሲማለስ ሚስቱ በሚናቅ ስሜቱ ውስጧእንደተጎዳ ነበር፡፡ እየሩስ ሰሚር ገና ከሚገባቱ ቀን የተፈጠረውን ነገር ዘርዝራ ነግራውወደ ቤቷ ሄደች፡፡ ኸሉድ መኝታ ቤት ጋደምብላ ታብሰለስላለች፡፡ ሰሚር ወደ መኝታ ክፍል ሲገባ ቁጣዋን በምን ቃል መጀመር እንዳለባት ታስባለች፡፡ ወደ መኝታ ክፍል እንደገባ "አሰላሙአለይኩምሁቢ!" አላት፡፡

"ሁቢ? እኔን ነው? ቀልደኛ!"

"ምን ሆንሽብኝ ደግሞ?"

"አንተ ስልክ እኔ ላይ ትዘጋለህ? ንገረኝ እስኪ ምን አይነት ንቀት ቢሰማህ ነው? ሰራተኛ

በሆንኩልህ? ራሴን ዝቅ አድርጌ በኖርኩልህ? ናቅከኝ! በጣምናቅከኝ! ስልክ ዘጋህ እኔ ላይ? ይገርሜል! በጣምይገርሜል!" እንባዋ አይኗን ሞልቶ ለመፍሰስ ያኮበኩባል።
"ኧረ ተይ ግን ኸሉድ ተይ! አንቺ ጠዋት ስወጣእኮ ያልሰደብሽኝ ስድብየለም፡ ሜሰሽ ደውለሽ ቁርስ ሳትበላ ምናምን ብለሽ ታሾፊብኛለሽ። ደሞታካሚአስቀምጬ ውስልክ ያነ ሳሁልሽ። የዘጋሁትምስራ ላይ እንደሆንኩነ ግሬሽ ነ ው።" ከአጠገቧ ተቀምጦ ግንባሯን ሳማት። ቁጣዋ ሁሉ ሲለያት ተሰማት።
ራሷን እየ ዳበሰ "ደሞዛሬ ከፎቁ ላይ ልትዘይ ነበር እንዴ?"
"እነ እየሩስ አሉኝ እኔ ግን አልገባኝም! የተኛሁ ነበር የማስለኝ።"
"ተናደሽ ነበር እንዴ?"
"በጣም!"
"ለዛ ይሆናል በቃ ተረጋጊ። ደሞእዚህ ብቻሽን መዋሉ ሳይሆን አይቀርምየ ሚረብሽሽ ስራ መጀመር አለብሽ!"
እሷ ቀድማየ ወሰነ ችውቢሆንምእንዳላሰበበት ሰው"ካልክ እሺ።" አለችው።

ግርዶ

ክፍል ስድስት

.

ረቡዕ ማክሰኞ ማለፉን ለማብሰር ይሁን ማክሰኞን ለማብሸቅ ባይታወቅምክረምቱን አብያ በፀሀይ ውበት ተፍነ ክንካለች። ዩስራ የእናቷ ከሁሉምጋር ማ ጋገር ማቆምበጣምአስጨንቋታል። ከሰኞ ማታ በኋላ ከሰሚራ ጋር ብቻ ነበር የምታወራው። የዘቢባ እና የዩሱፍ ትካዜ ውስጧን ስለረበሸውከቤት ለመውጣት የኢስማኢል ቀጠሮ ሁነ ኛ ምክንያት ሆኖላታል። ኢስማኢል የተቀጣጠሩበት ቦታ የደረሰው በሰዓቱ ነበር። እሷ ትንሽ ዘግይታ ፒያሳ ደረሰች። ሰዓቱ አስር ሰዓት ተኩል ሆኗል። ስለ ምርቃቱ አንዳንድ ነገር ካወሩ በኋላ ቅዝቅዝ ስትልበት ወደ ሚኪና ውሄደውእንዲያወሩ ጠየ ቃት። ተስማማች። ቪትዝ ሚኪና ውውስጥ ከኋላ ገብተውከተቀማጡ በኋላ አይኖቿን በስስት እያየ "ዩሳ ምን ውምን ሆነ ሻል በጣምየተረበሽ ይማስላል። ምን ተፈጠረ?" አላት። ልቧ ውስጥየተፈጠረውየሀዘን ጥላሸት ፊቷን ማደሙ ብዙምለእሷ ግልፅ አልነበረም፡ እንደተረዳት ስታውቅ አይኗን ሰበር እንዳደረገች የዘቢባ እና የዩሱፍን ሁኔታ ነገረችው። ልቡ ተነካ። "ደሞእኮ" አለች "ደሞእኮ እኔ ከድሮምእንደሚዋደዱ አውቅ ነበር አንተ እኮ ስለማታውቃቸውነ ው" እያለች መነሰቅሰቅ ጀመረች። ኢስማኢል ወደ ደረቱ አስጠግቶ አቀፋትና ያባብላት ጀመር። ሲያባብላት ነ ውማስል ይባሱን ማ ፋረቅ ጀመረች። እያባበለ ጉንጯን ሳማት። ትንሽ ረጋ ስትል "እንዲህ ሆነ ሽማቤት አትሄጂም! እኛ ቤት ትንሽ ተረጋግተሽ እሸኝሻለሁ!" አላትና ወደ መኖሪያ ቤቱ ሚኪናውን ነዳው። መኖሪያ ቤቱ እንደገቡ እሷ ረጋ ብትልም በማበል ስምየ ሜይነ ካውየ ሰውነ ቷ ክፍል አልነበረም፡ አሁን ሰውለማበል ጡት ይነ ካል? ዳሌው ቸብ ሲደረግ የተፅናናስ አለ? ከሀዘኑ ስሜት ወደማታውቀውና ወደማትፈልገ ውስሜት ተዘዋወረች። ፊቷ ተንቦገቦገ። ልታስቆመውፈልጋለች ግን ቀድሞራሷን ማከላከል በማትችልበት ስሜት ውስጥ ከቷታል። ከዚህ በኋላ ቤቱ ነውና ምንምይሉኝታ ሳይዘውከንፈሯን ማሳምልብሷን ሜውለቁን ተያያዘው። እሷ ተነክታ አታውቅምና ለመቅለጥ ብዙ ንክኪ አላስፈለጋትም፡ ወደ ሌላ ወደማታውቀውአለምተጉዛለች።

.

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ወደ ራሷ መመለስ ስትጀምር የነበረችበትን ሁኔታ መቀበል ከበዳት። ኢስማኢል እኮ ለሷ የፈጣሪን ሜዕክት በዜማየ ሚሰብክ ቅዱስ ሰውነ ው። ራቁቱን ከጎኗ ስታገኘው፤ ጫኗ በደም ሜጨማለቁን ልብስ ትል ግራ ገባት። አልጋውላይ እንደተጋደመች። "ኢስማኢል?" አለችው።
"ወዬ የኔ ንግስት"
"ምንድነ ውየ ተፈጠረው? ማለቴ ለምን እንደዚህ ሆነ?"
"ፍቅር ነዋ ውዴ! ፍቅር የሁሉምማሳረት አይደል አፈቅርሻለሁ!" ግንባሯን ሳማት።
"ኢስማኢል?"
"ወዬ?"
"ሳትን መነገድ የሚለውን ነሺዳህን በልልኝ እስኪ!"
በደስታ መነፈስ ወደ ራሱ አስጠግቶ አቀፋትና ማ ሸድ ጀመረ።
"መነገድ ጠፉን ፣ ሳትን መነገድ፣

ከእውነት ጋር የሚጣጣም፣ የሚዋደድ።
እዝነትህ ላይ ተንጠልጥለን ፣ ያንተን ቁጣ ዘንግተናል፣
ወንጀል ሰርተን አይከፋንም፣ እንላለን ይምረናል።
መንገድ ጠፋን ፣ ሳትን መንገድ፣
ፍርሀት አዝሎ፣ አንተን 'ሚወድ።
ፊትህ መቆም፣ እንዴት ሆኖ ይታሰባል፣
ማውራት ላንችል ፣ ወንጀል በዝቶ አፍኖናል።
መንገድ ጠፋን ፣ ሳትን መንገድ፣
ከእውነት ጋር የሚጣጣም፣ የሚዋደድ።
ህሊና ቢስ ፣ ሆንን ከንቱ፣
እምነት ጠፋን ፣ ማስረቱ።
ከልባችን እሾህ ሞላ ፣ ክፋት ዘራን፣
ምላሳችን ስምህን ጠራ፣ ያንተ ማስልን።
ቀን አለ አይደል ማስብሰቢያ ፣ ካንተ ሸንጎ፣
አካላችን 'ሚያወራበት ፣ አፍ ታሽጎ።
የእሳት ራት ፣ ምኞት አልባ፣
አካላችን ሲቀጣጠል ፣ ከእሳት አምባ፣
ሚረን ሚረን ፣ እኛ ከንቱ፣
ይቅርታህ ነው፣ የኛ ሰላምማስረቱ።
መንገድ ጠፋን ፣ ሳትን መንገድ፣
ከእውነት ጋር የሚጣጣምየ ሚዋደድ። "የሚለውጋር ሲደርስ ፊቷ ሁሉ በእንባ እንደታጠበ "በቃህ ኢስሜኢል! በቃህ።" አለችው፡፡ የሷ ልብ ክፉኛ ተረብሿል። "እንዴት ፈጣሪን ይፈራል የሚባል ፣ ስለሱ የሚዘምር ሰውእንዲህ ያደርገኛል? የሚዘምረውነገር ለራሱእንኳ አልገባውምማለት ነው?" ልቧ ውስጥ ብዙ ጥያቄ ይመላለሳል። እሱ የማያውቀውበማያምር ሜልኩ ዜማማቀለፁን ብቻነው፡፡ ግጥሙ ለእሱ ምንምነው፡፡ ግጥሙላይ ያለውየፈጣሪ ፍራቻ እና ፍቅር የሱ ህይወት ውስጥ ፍፁምየለም፡ ሳያስበውከመንፈሳዊ ህይወት ላይ ወደቀ እንጂ ከሜዜምየዘለለ ሀይማኖታዊነት እሱነቱ ውስጥ የለም፡ እስከዛሬ መድረክ ላይ ስለ ፈጣሪ ያወራቸውና የዘመራቸውነገሮች ሁሉ አስጠሏት። ኢስሜኢል ቀፈፋት።
"ኢስሜኢል?" አለችው
እቅፉ ላይ እንዳለች ፀጉሯን እያሻሸ "ወዬ የኔ ንግስት?"
"የምትነሽደውነ ሺዳ ትርጉምግን ይገባሀል?"
"እንዴት አይገባኝም? ግጥሙን እኮ ገጣሚዎቹ ሲሰጡኝ ማሻሻያ ሁሉ አደርግበታለሁ። ለዜማእንዲመች"
"ታዲያ አሁን የነሸድክልኝ ነሺዳ ትርጉምምንድነው?"
"ፈጣሪን መውደድ እንዳለብን ነዋ!"
"በቃ? እና አንተ ትወደዋለህ?"
"እና ባልወደውስለሱ እነሽድ ነበር?"
ውስጧእልህ ተቀጣጠለ። ከእቅፉ ወጥታ ከወገቧ ቀና ብላ ተቀመጠች። "ስማ ፈጣሪን መውደድ ማለት ለትዕዛዙ እጅ ማስጠት እንጂ የከለከለውከባድ አጥር ውስጥእየተመላለሱ ስለሱ ባዶ ቃላት መደርደር አይደለም፡ ብትወደውኖሮ

በዚህ ሁኔታ ሆነን 'ሳትን መንገድ' የሚለውን ነሺዳ ነሽድልኝ ስልህ ይከብድህ ነበር! አንተ ስለ ዜማውእንጂ ስለ ትርጉሙምንምአታውቅም፡ ፈጣሪ በተግባር የሚወደድ እንጂ በቃላት የሚሸነገል አይደለም፡" እንባዋ ፊቷን እያራሰ ሳጓ ድምጿን እያነቀ ቀጠለች "እንዴት አንተ እኔን እንዲህ ታደርገኛለህ? እኔ እኮ ፈጣሪን ትፈራለህ ብዬ አስቤነውያለስጋት ቤትህ ስትወስደኝ ዝምያልኩት። ሲጀምር እንደሌላውሰውባስብህ ብቻህን እንኳን ቤትህ ፣ ሌላ ቦታምአላገኝህምነበር። አንተ ፈጣሪን ተወውእሺ አታውቀውም! ለክብርህ አታስብም?" ኢስሜኢል ሊያረጋጋት በማስብ ከወገቡ ቀና ብሎአቀፋትና "ዩሲ ፕሊስ ተረጋጊ! ደስ ስለምትይኝ ነውእንጂ አብሮኝ ለሙተኛት የሚመጣኝ አድናቂ ጠፍቶ አይደለም፡ ላንቺምክብር እንጂ ውርደት የለውም፡ ባይሆን መገደርደሩን ተይና

እንድገ ሜው" ብሎ ሊያጋድሜት ሲሞክር እጁን ሚ ጨቃ ተነሳች።
ልብሷን እየለበሰች "ስማአንተ በጣምቆሻሻ ነህ እሺ! ስህተትህ እንኳ የሚይገባህ ደነዝ! ከዚህ በኋላ አጠገቤ ብትደርስ አዋርድሀለሁ! ውሻ!" አለችና ልብሷን ለባብሳ ደሟጬ ስር እንደፈሰሰ ቤቱን ከፍታ ወጣች። ኢስሜኢል ስትወጣበንቀት አይን እያያት "ሚኮተሽ ትለምኚኛለሽ ቆይ! ከብት!" አለ። ለእርሱ ይሄ ምንምሜላት አይደለም፡ በዚህ ሜልኩ ብዙ ሴቶች ጩቹ ስር ተሜልሷል። ብዙዎቹ ከዚያ በኋላ ይለማማጡትና ሲሜራቸውከሀገር ይጠፉለታል። የጋብቻ ተስፋ እየሰጠየ ሴቶችን ክብር እና ገንዘብእንዳሻውተምነ ሽንሾበታል። ታዋቂ ነው፡ ጌታውን ከማነምበላይ እንደሚፈራ ነ ሺዳዎቹ ምክክር ናቸው፡ ሴቶቹምከፈጣሪ ውጪለማነምአቤት የማላት ድፍረት የላቸውም፡
.
ዩስራ ቤት እንደደረሰች ወደ ሻወር ቤት ገብታ ገላዋን ታጠበች። ፈጣሪ ሀጥያቷን ከደሟጋር አብሮ በውሀውቢያፀዳውምኞቷ ነው፡ እንባ እንባ አላት። ተስፋ እንደሜቁረጥአለችና ተሜልሳ ከፈጣሪዋ እዝነት ተስፋ ሜቁረጥእንደሌለባት አሰበች። "በኢስሜኢል እጅ ምን ያህል ሴቶች ረክሰውይሆን?" ስትል ራሷን ጠየቀች። ሰውነቷን አደራርቃ ወደ ሜኝታ ክፍሏ ገባች። የዛሬውን ጉድ ለማነም ልትተነፍሰውአይቻላትምና በብዙ የሀይሜኖት ሰውተብዬዎች የሚፀሙብልግናዎችን እያሰበች ግጥም ሜፃፍ ጀሚሪች።
"ስሜቱ ማምለክ ነግሶ ፣ ከእምነት ጋር ተለውሶ፣
የቃቢልነት ጥሜት ሊያረካ ፣ የሀቢልነትን ካባ ለብሶ፣
ቃልህን እያነበበ ፣ በስምህ እየሜለ፣
ለጥፋት ተሜቻቸ ፣ ስንቱ ቢላውን ሳለ!
አንተን ሊያምፅ ፣ ሊሸሽ ካንተ፣
ባንተ ታንኳ ተሳፈረ ፣ ካንተ ጦር ውስጥተከተተ።
በሜዘኛህ ጨክነበት ፣ በሜቅረቢያህ አራቀበት፣
በሜንቢያህ አጠፋበት ፣ በነብሱ ላይ ፈረደበት።
ሊሸሽ ሊሸሽ፣ ሊሸሽ ሜጣ፣
በእዝነትህ ሊያስቆጣ፣
ሊሸሽ ሊሸሽ ፣ ሊሸሽ ሜጣ።
ከታንኳውላይ የተጫኔ ፣ ሀጥዕ ማነነት አለ፣
ሜዕበልን የሚጠራ ፣ ለሜጥፊያችን የተዶለ።
ሜክሜጥሆነ የኛ እድል ፣ ወንጀለኛ ዳኛ ሆነ ፣
ክልከላህን አዳረሰ ፣ ባንተ ቃላት የታሜ ።
ክብር ጠፋ ፣ እውነት ሸሸ፣
ያልነጋውቀን ፣ ዳግምሜሸ።
ሊሸሽ ሊሸሽ፣ ሊሸሽ ሜጣ፣
በእዝነትህ ሊያስቆጣ፣
ሊሸሽ ሊሸሽ ፣ ሊሸሽ ሜጣ። "
በግጥሙውስጥ ብዙ ኢስሜኢሎችን አሰበች። ሰዓቱ ወደ ምሽቱ አንድ ሰዓት ተቃርቦ ስለነበር እንደተለሜደውየዩሱፍ ሜኪና ጥሩምባ ተሰማ፡ ዩሱፍ እና ዘቢባ ቀኑን ሜሉ ሲያውጠነ ጥኑት የነበረውን ማሳሜኛ ከወ/ሮ ጀሜኢ ጋር ሊጋፈጡበት ተዘጋጅተዋል። ቤት ሲገቡ ሳሎን ውስጥ ወ/ሮ ጀሜኢ ብቻቸውን ተቀምጠዋል። ፊታቸውዛሬምአልተፈታም፡ ሁለቱምስሜዋቸውልብስ ሊቀይሩ ገቡ። ሲሜለሱ ዩሱፍ ዩስራ አለሜኖሯን ልብአለና ሰላምሊላት ክፍሏ ሄደ።

ዩስራ እያለቀሰች ነበር። ዩሱፍ በእነርሱ ምክንያት የምታለቅስ ሜስሎት አባበላትና ወደ ሳሎን ይዟት ሄደ። ወ/ሮ ጀሜኢ የሶስቱንምሜኖር ከተሜለከቱ በኋላ "እሺ የፊታችን እሁድ ከከሰዓት በኋላ እንግዳ ይሜጣል ስለዚህ በወጉ ማሳረት ተዘጋጁ!" አሉ። አልገባቸውም! "ምን አይነት እንግዳ?" አለ ዩሱፍ።
"ለኢድሪስ ቤተሰቦች ሽማግሌ እንዲልኩ ነግሬያቸዋለሁ። እሁድ ሜጥተውየኒካሁን ቀን እንቆርጣለን። " ዩሱፍ እና ዘቢባ ድርቅ ብለውቀሩ። ዩስራ ሜልቀስ ጀሚረች። ዩሱፍ የእናቱን አይን እያየ "እቴቴ እኛ ላይ ለምን እንዲህ ጨከንሽ? እኛ በወጉ ማሳረት ይሁን ብለን እንጂ እኮ ..."

አቋረጡት "እኮ ምን? ትዕዛዜን ወዲያ ብላችሁ ትጋባላችሁ?" አሉ። ዩሱፍ ዝምአለና "ቆይ ምክንያትሽ ምንድነ ው?" አለ። "በባህላችን ማክረት ሰባት ዘር ማላያየት አለበት። እንኳን የወንድምልጅ ቀርቶ ከአንድጎሳ መጋባት አይቻልም፡" አሉ።
"ከባህል እምነት አይቀድምም? እምነታችን እኮ በግልፅ ይሄን ይፈቅዳል። እባክሽ እቴቴ ደስታችንን አትቀሚን!" ዩሱፍ የሚጨፈሻ ተስፋ አልባ ልመናውን አቀረበ።
"እናቴ ነሽ ካላችሁ ማታዘዝ ነው። ጨርስኩ!" ዘቢባ የወ/ሮ ጀሚላ ውሳኔ እጅግ አበሳጭቷታል። አንደበቷ ሁሉ ተሳሰረ። ዩስራ እንደምንምራሷን አረጋግታ "እቴቴ ላንቺ ባህል የእነ ርሱ ህይወት ከሚበላሽ ባህሉን ጣሺውና እምነትሽን አክብረሽ ቤታችን ይድመቅ!" አለች። ወ/ሮ ጀሚላ በንዴት ፊታቸውእየተንቦገቦገ "ዝጊ አንቺ! ህፃን!" አሉና "ስሚደግሞዘቢባ ከዚህ በኋላ ከዩሱፍ ጋር ስራ ሜድ አያስፈልግሽም! ቤት ውስጥእረፍት ማድረግ አለብሽ። ለስራውእርሱ ይበቃል!" አሉ። ሀሳባቸው ሁለቱን ማላያየት ሚሆኑ ለሁሉምግልፅ ነበር። አሁን ያላቸውአማራጭየ ዘቢባ እናት ጋር ደውሎ ጋብቻውእንዲቆምማስደረግ ብቻ ነው። ወ/ሮ ጀሚላን ማሳመን የማይሆን ሚሆኑ በደንብ ተገልጦላቸዋል።
***

.
ይቀጥላል

ግርዶ

ክፍል ሰባት(7)

.
ሰሚር የሚኪቱ የፀባይ ማላዋወጥ ምክንያት ጭንቀት ሊሆን እንደሚችል አስቧል። ቤት ውስጥ በመዋሏና የረባ ጓደኛምባለመኖራቷ ለጭንቀት ተጋልጣለች የሚል እሳቤ ከልቡ አድሯል። የዛሬን አያድርገ ውና ቤታቸውየ ፍቅር ተውኔት የሚታወንበት መድረክ ፤ ፍቅራቸውደግሞሁሉንምየ ሚያስቀና ነበር። ሰሚር የመጀመሪያ ቀን ያገኛት እሱ የሚሰራበት ሆስፒታል ለትምህርታዊ ልምምድ በመጣችበት ጊዜ ነው። ታዲያ ውበቷ ያኔ ምሆነ ዛሬ እጅግ አማላይ ነው።
"ሰም?" አለችውከእቅፉ ውስጥ ጋደምእንዳለች አይን አይኑን እያየች። "ወዬ ፍቅር" ወደ ደረቱ አስጠግቶ ግንባሯን ሳማት።
"ዘቢባ ደህና ናት ግን?"
"እሁድ ስሄድ ደህና ነበረች። ምነ ው?"
"አይ ደህና ትሁንልህ!" ብላ በንዴት ከአልጋውተፈናጥራ ተነሳች። ሊያረጋጋት ቢሞክርምአልቻለም፡ "ድሮምእዛ ቤት የምትሄደውእሷን እንጂ ዩሱፍን ፈልገህ አይደለም! ሴሰኛ!" አለችው። ግራ ሲገባው ልብስ ደረብአድርጎ ከቤት ወጣና ኮሪደሩ ላይ ቆሞወደ ዩሱፍ ስልክ ደወለ። ዩሱፍ የተፈጠረውን ሁሉ አወጋው። ያለዘቢባ ወደ ስራ ሜድ በጣምእንደከበደውነ ገረው። ስልክ እያናገረ ትንሽ እንደቆየ ኹሉድ ጋቢ አምጥታ ጀርባውን እያለበሰችው"ከማሻ ምን ው? ሲነ ጋ አይደርስም? ብርድ እኮ ነው።"ብላ ከጀርባ አቀፈችው። ሰሚርና ኹሉድ የባልናሚስት የአልጋ ላይ ጀብዱ ከፈፀሙወር ሊያልፈውነ ው። ሰላምሆነ ውይቆዩና ወደ ጉዳዩ ሊዳረሱ ሲሉ ኹሉድ ፀባይዋ ይቀየ ራል። ሰሚር እጅግ ከባድ ፈተና ሆኖበታል። አሁን ግን ይሄን እድል ማጠቀምእንዳለበት ስላማ ከእቅፉ አድርጓት እየተሳሳሙወደ ቤት

ገቡ። ልብሳቸውን አውልቀውትንቅንቁ ሊጀምር የመጀመሪያውጡጫከሰሚር ሲሰነ ዘር ኹሉድ በንዴት ተፈናጥራ ከስሩ ወጣች። ሰሚር እጅግ ክፉኛ ልቡ ተሰበረ። አልቅስ አልቅስ አለው። ሚስት እያለው ሚስት አልባ ሚሆኑ አመመው። በግድ ገፍትሮ አልጋውላይ አስተኛት። እጆቿን በእጆቹ ከአልጋውጠፍሮ ይዞ በግድ ይገናኛት ጀመር። የእርሷ አካል በድን ሆነ በት። ትንሽ የቅንጡትምባይሆን የመተንፈስ ያህል እርካታ ካገ ኘ በኋላ ከላይዋ ላይ ተነሳ። ህይወቱ በጣምቀፈፈው። የሚከስ ፣ ክብር የማጣት ጭንቀት ወረረው። የመኝታ ልብሷን አልብሶ የአልጋ ልብሱን ገፎ ከስር አስተካክሎአስተኛት። ከአጠገቧ ሲተኛ ከደረቱ ልጥፍ ብላ አንገቱን ሳመችው። ውስጡተቃጠለ። የማትበላ ወፍ ሆነ ችበት።
.

ጠዋቱን ሰሚር ከቤት ሊወጣሲል ኹሉድን ብቻዋን ትቶ ሜድ በጣምስለከበደውበስልክ ሁሉንምነገር ለዘቢባ ካስረዳ በኋላ ቤታቸውአድርሷት ሄደ። ዘቢባ እና ኹሉድ በደንብ ይተዋወቃሉ። ግን ቅርበታቸውየሁለቱን ወንዶች ያህል የጠነከረ አይደለም፡
ዘቢባ ቤት የዋለችበትን የመጀመሪያ ቀን በኹሉድ አዳባሪነት ሲልምእርሷን በማከበቅ አሳለፈችው፡ ወደ እናቷ ያደረገችውየስልክ ጥሪ የጠበቀችውን መፍትሔይዞ አልተማለሰም፡ ወ/ሮ ከንዚያ የወ/ሮ ጀሚላ ሀሳብዋነኛ ደጋፊ ሆነውአረፉት። ይሄ ለዩሱፍ እና ለዘቢባ ከባድ ሚርዶነው፡ የማታወቀው ኢድሪስ በቤተሰቧ ተሚርጦላታል። እሁድ የኒካህ ቀን ሊቆረጥነው፡ ከኹሉድ ጋር ወጣብለውወ/ሮ ጀሚላ ያዘዟቸውን ነገሮች ገዛዝተውተማለሱ። እየሆነ ያለውነገር ሁሉ ፍፁምከቁጥጥራቸውውጪ ነው፡
***
እሁድ ጠዋት ላይ ዝናቡ ይነጫጫል። የአየሩ ሁኔታ የዩሱፍ እና የዘቢባን የልብትርታ ተማሳስሏል። አልቅሶ አይወጣላቸው፤ ፈክቶ አይተዋቸውእንዲሁ እኝኝኝ ብቻ! ዛሬ የታዋቂውሙሺድ ኢስሚኢል የነሺዳ አልበምይሚቃል። በጠዋቱ አንድ ላይ ከቤት ለመውጣት ሰበብስላገኙ ደስ ብሏቸዋል። በጊዜ ተዘገጃጅተውዩስራን ሊጠሯት ወደ ክፍሏ ሲሄዱ ቁጭብላ እያለቀሰች ነበር። ዩሱፍ በእነርሱ ምክንያት እንዲህ በሀዘን መጎዳቷ እያመመውአቅፎ አባበላት። እንደዛሬውክብሯን ሳይነካባት በፊት ለማስተባበር ገናኅህ ከመቅደዱነበር ወደ አዳራሽ የምትሄደው፡ ዛሬ ያ ሁሉ ብርታትዋ ተሰብሮ ስለ ክብሯ እየተንሰቀሰቀች ነው፡ ምርቃቱን ማታደምአልፈለገችም፡ ግን ደግሞለነ ዘቢባ የምታቀርበውምክንያት የላትም፡ እንደምንምበድኗን እየጎተተች የዩሱፍ ሚኪና ውስጥከኋላ ገባች። ሚኪናዋ ወደ ሰሚር ቤት ማታጠፊያ ስትደርስ ሰሚር እና ኹሉድ ቆመውእየጠበቋቸውነበር። ዘቢባ ከጋቢና ወርዳ ከኋላ ገባችና ሰሚር ጋቢና ገባ። ሶስቱ ሴቶች ከኋላ ተቀምጠውወደ አዳራሹ ሄዱ። የዩስራ ልብ ውስጥየኢስሚኢል ጥላቻ ከደሟጋር ወደ ሰውነቷ ይረጫል። "ዛሬ ደሞምን ይል ይሆን?" ብላ በልቧ ትጠይቃለች። ወደ አዳራሽ እንደደረሱ የሚያውቋት ልጆች ሚርፈዷገርሟቸው በጥያቄ አጣደፏት። ሁሉንምበቀልድ እየሸነገለች ወደ ውስጥገባች። ሰሚር እና ዩሱፍ በወንዶች ረድፍ፤ እነ ዘቢባ ደግሞበሴቶቹ ረድፍ ተቀመጡ፡ ዩስራ የአዳራሹን ድባብ በተማስጦአጤነችው፡ በሴት እና በወንድ አስተናጋጆች መካከል ያለውመጎነታተል ፣ መጎሻሸም፣ የወጣት ወንድና ሴት ታዳሚዎች መካጃጀል ሁሉምበግልፅ ይታያትነበር። ሰውየተለያየ ነገር ፈልጎ አንድቦታ ይሄዳል። ሰውስሜቱን ወላ ሴሰኝነቱን ለማስተናገድ የእምነት ተቋማት ወላ ሚድረኮች ላይ ይዶላል። ከዚህ አዳራሽ ውስጥየተገኘውምሰውየ ማጠበት አላማእጅግ የተለያየ ነው፡ ለምሳሌ እነ ዘቢባ የማጡት አብረውወጣየ ሚኑበት ሰበብ ስለሆነላቸውከቤት ለሚራቅ ብለው፤ ሰሚር ኹሉድን ይዞ የማጣው አለባት ብሎያሰበውጭንቀት ወጣስትል ከተዋት ብሎ፤ ዩስራ ደግሞየ ማጣችውየምትቀርበት ምክንያት ስለሌላትነው፡ ደግሞከታዳሚውመሀል ቆንጆ የቤት ልጅ ስልክ ቁጥር ለመቀበል የተገኘ ይኖራል። አንዳንዶቹ ሴቶች ደግሞየ ማጡት ከቤት ውስጥስራ ለማምለጥነው፡ ነሺዳ ስለሚወድ የተገኘምሊኖር ይችላል። ግን የተገኙበት ቦታ ከተገኙበት አላማጋር የሚይገጥምበርካታ ሰዎች አሉ። በለሆሳስ "የምንፈልገውሌላ የምንሄድበት ሌላ!" አለችና በአይኗ አዳራሹን ማቃኘቷን ቀጠለች። እንዲህ በጥሞና ለመሜልከት ጊዜ አግኝታ አታውቅም፡ ነገሮች በግልፅ የሚታዩት

ገለል ተብሎሲቆምነው፡ ገለልተኝነት የአእምሮ እርጋታ አለው፡ የመሜልከቻ ጊዜ ይሰጣል። ዝግጅቱ ተጀምሮ ታዋቂ ዳዒዎች ሚድረኩ ላይ ቆመውይሰብካሉ። ዩስራ በልቧ "ምናለ የሚኑት በገባውና ደነዝነቱ በተጣለው" ብላ ኢስሚኢል ላይ ትበሳጫለች። ስብከቱ ተጠናቆ ኢስሚኢል ወደ ሚድረክ ሲወጣ ጩኸት አዳራሹን ነቀነቀው፡ ብዙሀኑ ጯኺደግሞሴት ነው፡ ለነገሩ ነሺዳውን ሳይሆን ሙሺዱን ሊሚርቁ የማጡበርካታናቸው፡ አንዳንድቀበጥየሀብታምልጆች ታዋቂ ሰውማካበስ የትልቅነት ማሳያ ይማስላቸዋል። ከሰሙጫቸውሴትነታቸውን ተነጥቀውሲነቁ "እኔ አላህን ይፈራል ብዬ ብቀርበው" ምናምን እያሉ ይነፋረቃሉ። አላህን መፍራት የሚጀምረውጭን መሀል ይማስላቸዋል።
"የማትፈቀድለትን አንቺን አድናቆትሽን ለመቀበል ብቻሽን ቀጥሮ ያገኘሽ ቀን ነውአላህን የመፍራት ካባውን ያወለቀው" ብትላቸውአይገባቸውም፡ ስለፈጣሪ ዜማማቀኘት የፈጣሪ ፍራቻሳይሆን ውብድምፅ ብቻ እንደሚጠይቅ አይረዱም፡ የሜፈሻ የእውቀት ደረጃ ማታወቅ የሚማስላቸውከንቱዎች ናቸው፡ ዳኢ እና ሙሺድ እያሳደዱ እየተሞዳሞዱ፤ ጩናቸውበደምሲጨማለቅ "አላህን ይፈራል ብዬ" ብለው ያለቃቅሳሉ። "አንቺ የታዋቂነት ፈተና ሳይጩብሽ ያልፈራሽውን አላህ ፤ የታዋቂነት አዚም በእዩልኝ ሜስበል የሚጣቸውእነሱ እንዴት ይፍሩ?" ብትላቸውይድረስብንና እንሚር ይሉሀል።

ስለነ ብዩ መሀመድ (ሰዐወ) ውብ ስብዕና ያወራ፣ የነ ሸደ እና የገጠምሁሉ መሀመድ የሚሞትለውማጦሪያ አልባ ትውልድ፤ ከትውልድ ታንኳውላይ እኒ ህን ግለሰቦች እያነ ቀ ወደ ባህሩ ካልወረወረ ቀስ በቀስ ማስማጡነ ው። ዩስራ ከጭብጨበውየ ተስተጋባውድምፅ የፈጠረባት ንዴት አእምሮዋን ክፉኛ ሲወዘወዘውየ ተፈጠሩ ቁጭቶች ነ በሩ። ኢስሜኢል ሙድረኩ ላይ ወጥቶ አዲስ ከለቀቀውነ ሺዳ ውስጥ "ሳትን ሙነገድ" የሚለውን ነ ሺዳ ተጫወተ። ከፊሉ የነ ሺዳውን ሜልዕክት እየ ሰማያነ ባል። ኢስሜኢልምፊቱ በሀዘን ድባብ ተውጧል። ልቡ ግን በማስለቀሱ እየ ተደሰተች ይሆናል። "እኔ ን ከሙድፈር ባልተናነ ሰ ሜልኩ ክብሬን በቀማበት ቀን ይሄን ነ ሺዳ በሙጀቢያነ ት ዘፍኖታል ብል ማን ያምነ ኛል?" አለች በልቧ። ኹሉድ እና ዘቢባን ዞር ብላ ስትሜለከታቸውእያነ ቡነ ው። እርሷ ምግቡ የቀረበበት ሳህን የሙብላት ፍላጎ ቱን እንደዘጋውሰውሁሉ ነ ሺዳውሜልዕክቱ ምንምሜልካምቢሆን የ ኢስሜኢል ማነ ነ ት ነ ሺዳውግድ እንዳይሰጣት አድርጓታል። ከዚህ በላይ ሙታገ ስ ስለከበዳት አዳራሹን ለቃ ወደ ዩሱፍ ሚኪና ሄደች። ደውላ ቁልፍ ከተቀበለችውበኋላ ሚኪናውውስጥ ተቀምጣ ተንሰቀሰቀች። የቀሜት ክብር አለ። የሜይሜለስ ክብር!

*

ዩሱፍ፣ ዘቢባ እና ዩስራ ወደ ቤት ሲገቡ ሳሎኑ ውስጥ ጋሽ ከሜል እና ወ/ሮ ጀሚላ ከጎረቤት አቶ አህመድን ጨምሮ ውከማጡት ሽማግሌዎች ጋር እየ ሜከሩ ነ በር። ዩስራ እና ዘቢባ በኋላ በር ወደ ሜኝታ ክፍላቸውገ ቡ። ዩሱፍ በዋናውበር ገ ብቶ ሁሉንምሰላምካለ በኋላ አብሯቸውተቀሜጡ። "ስለዚህ ኒካውከሁለት ወር በኋላ በጳጉሜይሁን!" አሉ ወ/ሮ ጀሚላ! ሁሉምበሀሳቡ ተስማምተውጳጉሜ4 ኒካሁ እንዲደረግ ተወሰነ ። ዩሱፍ ዝምብሎ ከተከታተላቸውበኋላ ምሳ ለማስቀረብ ተነ ስቶ ወደ ሚድቤት ሄደ። ውስጡላይ የተፈጠረውን ህሜምበምንምሊያበርደውየ ሚችል አልማሳለውም።
ምሳ ተበልቶ ሲያበቃ ሽማግሌዎቹ ተሸኙ። ዩሱፍ ወደ ዘቢባ ክፍል ሄዶ የተወሰነ ውን ሁሉ ነ ገ ራት። አንድ ነ ገ ር ሙድረግ አለባቸው። አለበለዚያ ግን ይህን ሁሉ አሜት የገ ነ ቡት የፍቅር ጎጆ ህጋዊ እውቅናን እስከወዲያኛውሜ ሳቱ ነ ው።
"ዘቦ?" ዩሱፍ አልጋዋ ላይ ተቀምጦ በስስት እያያት ትኩረቷን እንድትሰጠውያደረገ ውጥሪ ነ በር።
"ወዬ?" ዘቢባ ከጭንቀቷ ለሙውጣት እየ ታገ ለች ሜለሰች።
"ይኼን ጋብቻ ማስቆምየ ምንችለውበምን ሜልኩ ነ ው?"
ጋደምካለችበት ትራሷን ቀና አድርጋ ተስተካክላ እየ ተቀሜጠች "በቃ እንጥፋ!" አለችው። ይኼን ሀሳቧን ዩሱፍ በፍፁምእንደሚይቀበለውለእሷምግልፅ ነ በር። እናቱን በጣምይወዳታል። ትቷት ሜሄድ ፍፁምአይቻለውም።
ዩሱፍ ትንሽ እንደሜኾኮርሙምካለ በኋላ "ዘቦ ከኔ አርግዘሻል ብንላቸውስ?" አለ።
"ልንዋሽ?"

"አዎ የእውነ ት ከምናደርገ ውአይሻልም?"
ሁለቱምጥልቅ የሆነ ሀሳብውስጥሰጠሙ። እንዲህ ያለ ነ ገ ር ስለሙድረግ አስበውአያውቁም። ውሸቱን ለሙተወን ተስሜሙ።

*

ይቀጥላል ...

ግርዶ

ክፍል ስምንት

.

ሰሚር በጠዋቱ የንጋት ስግደትን ከውኖ እንደተሜለሰ ከኹሉድ ጋር ሜጨዋወቱን ወዶታል። "ዛሬ ከጭንቀቷ ሜኡ ለሜኡ ፀድታለች!" ሲል አሰበ። ውቧን ተጨዋቿን እና ተንከባካቢዋን ኹሉድን አግኝቷታል። ሰኞ ስለሆነ በጊዜ ስራ ለሙግባት ቁርስ በልቶ ሚኪቱን ተሰናብቶ ወጣ።
ኹሉድ ትንሽ ከተቀሜጠች በኋላ ወደ ዘቢባ ለሜሄድ አስባ ሜለባበስ ጀሚረች። ከቤቷ ወጥታ ከሰፈራቸው ትንሽ ራቅ ብሎ ወዳለውየ ሁሴን ቤት ሄደች። ሁሴን በርካታ ጊዜያትን ለትዳር ሲለምናት የነ በረ ሰውነ ው። በሚሀል ሰሚር ሙጥቶ ህልሙን ነ ጠቀው። ሁሴን ሙምጣቷን ሲሜለከት በደስታ ተቀብሎ ወደ ቤቱ

አስገባት። ትንሽ ከተጨዋወቱ በኋላ ወደ መኝታ ክፍሉ ይዟት ገባ። ተፈተለ ፣ ተሸማ ። ከእቅፉ ውስጥ እንዳለች ያለችበትን በታስታስተውል ደነገጠች። የሁሴን እቅፍ ውስጥ እንዴት እንደገባች ለሷ ግልፅ አይደለም። ራቁቷን መሆኗን ስታስተውል በጣም ጩኸቅ አላት። ሁሴን በእርካታ መንፈስ ደረቱ ላይ ልጥፍ አድርጎ ግንባሯን ሳማት። ድንጋጤዋን ለመደበቅ እየሞከረች "በቃ ልሂድ እሺ?" አለችው።

"ምን ውትንሽ አትጫወቺም?" አብራውቀኑን ብትውል ደስተኛ ነው።

"ስራ አትገባም እንዴ?"

"አለቃ የለብኝም። ሰራተኞቹ ስለሚከፍቱ እኔ ቀስ ብዬ ነው የምሄደው!"

ተነ ስታ ልብሷን ለባበሰች። ሊሸኛት ተነ ሳ። ልቧ በድንጋጤሊፈነ ዳ ምንምአልቀረውም። አትሸኘኝ ብትለውምሁሴን በፍፁምእሺ ሊል አልቻለም። መኪናውን አስነ ስቶ ወደ ኮንደሚኒየምቤቷ አደረሳት። ከመኪናውስትወርድእጇን ያዝ አደረገና ወደ ራሱ ጎትቶ ከንፈሯን ሳማት። እምቢ ለማለት የሚያስችል ድፍረት ውስጧየ ለም። አብራውመተኛቷ ያለማምመብቷን አሳልፎ እንደሰጠአምኗ ለች። ሁሴን ከኪሱ የ ታሸገ አስር ሺህ ብር አውጥቶ "ለአንዳንድ ነ ገር ይሆንሻል!" ብሎ ቦርሳዋ ውስጥ ከተተላት።

ስልኳን ተቀብሎ ወደ ስልኩ ደወለ። ስልክ ቁጥሯ አልነ በረውም።

ከመኪናውወርዳ ጥቂት እንደተራመደች ከአይኗ የእንባ ጎርፍ ተንደረደረ። ፊቷ ፍምመሰለ። ጥቅም አልባ ርካሽነ ት ተሰማት። "ሰሚሬ ዛሬ ያስደፈርኩበትን መብቱን ቢያውቅ ምን ይላል?" ከራሷ ጋር መግት ገጥማለች። ቤቷ እንደገባች ገላዋን ታጥባ የትዳር አልጋቸውውስጥ ተኛች። የአልጋውን ፅህና የአካሏን ጉድፍ ቢያጠራውትመኛለች።

*

ዩስራ የደረሰባት ማሰበር እያደር ባሰባት እንጂ አላገገማም። እየፈካ የነበረውየ ህይወቷ ፀሀይ በድንገተኛ ደመና ሀይሉ ሲዳከምና ሲጨፈግግ ህይወቷ ትርጉምአጣበት። ከጠዋት ጀምሮ ከመኝታ ክፍሏ አልወጣችም። ነ ሺዳ አታዳምጥነ ገር ሁሉምነ ሺዳዎች ዘረውዘረውኢስሚኢልን እያስታወሷት ተቸገረች። ከላፕቶፒ ላይ ሁሉንምነ ሺዳዎች አጥፍታ በምትኩ ቁርዓን ማዳመጥ ጀምራለች። "ሰውሲገፋ ወደ አምላክ እንጂ ወደ ማንምአይሸሽም!" ትላለች። የቁርዓኑ ሁሉምአንቀፆች ስለሷ እየ ማሳኗት በከፊሉ ተስፋ እየሰነ ቀች ፤ በከፊሉ ትበረግጋለች። ዘቢባ የመኝታ ክፍሏን በር አንኳክታ ስትገባ ዩስራ እንባዋ እየፈሰሰ ነ በር። ዘቢባ ተደናግጣ"ዩስሪ ምን ሆንሽብኝ በአላህ?" አለች። ዩስራ ፈገግ ለማለት እየሞከረች ቁርአኑን አጠፋችውና "ትንሽ ስለራሴ እያሰብኩነ በር!" አለቻት። ዘቢባ ፈገግ ብላ "ለውጥ ይሉሻል ይሄ ነ ው። ከዛ ልጅ ጩኸት በአንዴ ወደ ቁርዓን ደስ ይላል!" አለች። ከዚህ በፊት ነ ሺዳን ጩኸት ስትላት ትናደድነ በር። ዛሬ ግን እንደውምደስ አላት። ዘቢባ ከዩሱፍ ጋር ያወሩትን ለዩስራ አጫወተቻት። ዩስራምዘቢባ ያረገዘች ሴት የምታሳያቸውን ባህሪያት ማሳየት

እንድትጀምር መከረቻት።

ዘቢባ ከዩስራ መኝታ ቤት ስትወጣዩስራ "እና እንዴት ነ ውከዩሱፍ ተነ ጥሎ ቤት መዋሉን እየ ለመድሽው ነ ው?" ብላ ሳቀች።

ዘቢባ ሜስ ሳትሰጣት እየሳቀች ሄደች። ወ/ሮ ጀሚላ ያሉበት ክፍል ጋር ስትደርስ ሆነ ብላ የ ማቅርሸት ድምፅ ማውጣት ጀመረች። ወ/ሮ ጀሚላ ደንግጠውደግፈውወደ ማታጠቢያ ቤት ወሰዷት። የ ማስመለስ ድምፅ ታወጣለች ግን የሚወጣነ ገር የ ለም። ወ/ሮ ጀሚላ ጠረጠሩ። ግን ጥርጣሬያቸውን ይፋ ማውጣት አልፈለጉም። አንዳንዴእንዲሆን የ ማንፈልገ ውነ ገር እየሆነ ሲመስለን ፤ እየሆነ መሆኑን አምን ን መናገ ር አንፈልግም። ንግግራችን ድርጊቱን የሚያሳካውይመስለናል።

*

የዩሱፍ እና ዘቢባ ውድ ቀን እሁድ ደረሰች። እሁድ ዘቢባ እና ዩሱፍ በቀን የሚገናኙበት ብቸኛ ቀን ከሆነ ሁለት ሳምንት ሊሆነ ውነ ው። ጠዋቱን ዘቢባ የእርግዝና ትወናዋን በማቅርሸት እና በማ ጭጩ ጬ ስትከፍት የወ/ሮ ጀሚላ እልህ ተሟጠጠ። "ዘቢባ!" አሉ ቁጣበተቀላቀለበት ድምፅ። አፏን እንደማጥራረግ እያለች "ወ ዬ" አለችና እርሳቸውወዳሉበት ክፍል ሄደች። ወ/ሮ ጀሚላ በጠዋቱ ቡና እየ ጠጡነ በር።

ትክ ብለውተመለከቷትና "አንቺ ዩሱፍ ነ ክቶሽ ያውቃል እንዴ?" አሉ።

"መንካት ማለት?" የ ሚሉት በደንብ ቢገ ባትምትወናውን ለማካካት በሜላ ጠየ ቀች።

"አብራችሁ ተኝታችሁ ታውቃላችሁ?"

ዘ ቢ ባ የ ድን ጋ ጤ የ ሚ በሽ ስ ሜቱ ለማሳየ ት ሞከረች። የ ዘ ቢ ባ ሁኔ ታ ወ/ሮ ጀሚላ ጥር ጣሬ ያ ቸው
እ ውነ ት መሆኑን ወደሚ ጋ ገ ጡ ሲቀ ር ብባ ቸው"ን ገ ሪኛ! ታውቃላ ችሁ ወይ!?" ቁጣቸውከገ ፃ ቸው
ይነ በባል።
አ ን ገ ቷን በት ን ሹ በአ ዎን ታ ነ ቀነ ቀችው፡ ወ/ሮ ጀሚላ ድርቅ ብለ ውቀሩ። "ጥሬ ከፊቴ!" አ ሏት
ን ዴታቸውእ ሷን ወደ ሙ ዳት እ ን ዳ ያ ደር ሳ ቸውፈር ተው፡
ዘ ቢ ባ ወ/ሮ ጀሚላ ካ ሉበት ክ ፍል ወጥታ የ ትወና ዋን ውጤት ለ ዩ ሱፍ ለ ማበሰ ር ወደ ክ ፍሉ ሄ ደች። ዩ ሱፍ
ተቀ ምጦ ሂ ሳ ብ እ የ ሰ ራ ነ በር ። ገ ብታ ከአ ጠገ ቡ ከተቀ መጠች በኋላ ከደቂ ቃዎች በፊት የ ተፈ ጠረ ውን
ሁሉ ነ ገ ረ ችው፡ ሁለ ቱም ጮክ ብለ ው ሳ ቁ። ዩ ሱፍ ፈገ ግ እ ን ዳለ "አ ሁን የ እ ቴቴ ቀ ዳ ሚ ስ ራ ሰ ር ጉን
ማሳ ረ ዝ ነ ው፡ ይሄ ደግሞ እ ን ድን ጋ ባ ባትፈ ቅ ድልን እ ን ኳ ጊ ዜ ስ ለ ሚ ዛ ልን ሌላ እ ቅ ድ ለ ማውጣት
ይረ ዳ ና ል። " አ ለ።
"ቀጣዩ እ ቅ ድ ምን ድነ ው?" ዘ ቢ ባ ነ በረ ች
"ቀጣዩ እ ቅ ድማ'እ ን ጋ ባ ፍቀ ጅልን! ለሌላ ሰ ውከ ዳ ር ሽኝ ዘ ራ ችን ሊዋረ ድ ነ ው፡ እ ያ ልሽ እ ቴቴን
በደካማጎ ኗ ገ ብተሽ ለ ማሳ መን መሞከር ነ ው፡ "
ዘ ቢ ባ የ ማሽነ ፍ ስ ሜቱ ውስ ጧበደስ ታ እ ን ዲሞላ ሲያ ደር ገ ውተሰ ማት። ዩ ሱፍን "ባሌ" የ ምትልበትን
ቀን ና ፈቀች።
***
ሰ ሚር ከስ ራ ሲመለስ ኸሉድ አ ል ጋ ቸውላ ይ አ ን ቅ ልፍ ይዟት ጭል ጥ ብሏል። ሊረ ብሻት ስ ላልፈለገ
በጥን ቃቄ እ የ ተራመደ ከአ ጠገ ቧ ተቀ ምጦ ተመለከ ታት። አ ይኖቿ አ ባ ብጠውኳስ አ ካ ክ ለ ዋል። ከን ፈሯ
ወደ ፊት ተለ ጥጧል። አ ፍን ጫዋ ፣ አ ይ ኗና ከን ፈሯ ከወትሮውበተለየ ቀልተዋል። እ ያ ለቀሰ ች
እ ን ደነ በረ ገ ባ ው፡ "አ ሟቱ ነ በር ይሆን?" ሆዱን ባር ባር አ ለ ው፡ ትቷት በሜ ዱ ወን ጀለ ኝነ ት
ተሰ ማው፡ በዝግታ ግን ባሯን ሊስ ም ሲያ ጎ ነ ብስ ከእ ን ቅ ልፏ ነ ቅ ታ አ ይ ኗን ገ ለጠች። ጠየ ምያ ለ
ከን ፈር ታያ ት። በድን ጋ ጤ"ሁሴን!" ብላ በእ ጆቿ ከን ፈሩን እ የ ገ ፋች ከወገ ቧ ቀና አ ለ ች። ተረ ጋ ግታ
ስ ትመለከተውሰ ሚር ነ ው፡ ድን ጋ ጤዋ አ ር በተበ ታት። ሰ ሚር "ሁሴን?" አ ለ በውስ ጡ፡ ስ ሙለእ ሱ አ ዲስ
አ ይደለም፡ የ ተጋ ቡ ሰ ሞን በዚህ ልጅ ምክን ያ ት ስ ልክ ቁጥሯን እ ን ዳ ስ ቀየ ራ ት ያ ስ ታውሳ ል። "ሰ ሜ?"
አ ለ ች አ ይኖቿን አ ይኖቹ ውስ ጥ እ ያ ስ ለ መለመች።
"የ ኔ ን ግስ ት?" መለሰ
"ሁሌምቢሆን ካ ን ተ ሌላ የ ሚቅ ረ ውየ ለ ምእ ሺ! እ ወድሀ ለ ሁ ፣ አ ፈ ቅ ር ሀ ለ ሁ። ሁሌምያ ን ተ ብቻ ሆኜ
መኖር እ ፈልጋ ለ ሁ። " ን ግግሯ ከውስ ጧየ ሚፈልቅ ስ ለነ በር እ ር ጥበት ነ ካ ካ ውማካ ል እ ን ባዋ ከአ ይኗ
ወረ ደ።
"እ ኔ ሁሌምያ ን ቺው፤ አ ን ቺምሁሌምየ ኔ ው፡ ሁሌም!" ወደ ደረ ቱ አ ስ ጠግቶ ሲያ ቅ ፋት ከን ፈሩን
ሳ መችው፡ ፀ ባ ይዋ እ ን ዳ ይቀየ ር በልቡ እ የ ፀ ለየ ልብሷን አ ወለ ቀላ ት። አ ሁን ምበፀ ሎቱ እ ን ደበረ ታ
ነ ው፡ በግድ ማ ና ኘት፤ በድኗን ማሻ መን ሰ ልችቶታል። የ ተለ በሰ ውሁሉ እ ን ደ ቅ ጠል በስ ሜቱ እ ና
በፍቅ ር ተሙቶ ሲረ ግፍና አ ካ ል ከአ ካ ል ሲጣበቅ የ ሰ ሚር ፀ ሎት ተቀ ባ ይነ ት አ ለ ማግኘቱን
የ ሚያ ስ ረ ግጥ የ ኸሉድ የ አ ትን ካ ኝ ትግል ተጀመረ ። ትከሻውን ወደ ኋላ እ የ ገ ፋች ከላ ይዋ ላ ይ
ልታስ ነ ሳ ውታገ ለ ች። ሰ ሚር ቀልቡ ስ ብር እ ያ ለ ሁለ ቱን እ ጆቿን እ ን ደተለ መደውከራ ሷ በላ ይ
ከአ ል ጋ ውጠፍሮ ፤ ከእ ግሮቿ ር ግጫሸ ላ ል ኮ አ መለ ጠና ከመሀ ሏ ከተመ፡ በዚህ መልኩ በግድ የ ሚ ና ኛ ት
ቀን ኸሉድ መሆኗን ማመን ይቸግረ ዋል። ጉልበቷ ጉልበቱን እ ጅግ ይፈ ታተነ ዋል። "ሚስ ቴ እ ን ደዚህ
ጠን ካ ራ ና ት እ ን ዴ?" እ ያ ለ ከራ ሱ ጋ ር መሟት ይደግሳ ል።
ተገ ና ኝ ቷት መለ ፋቱ ሲደክመውምና ልባ ትምሲረ ካ ከላ ይዋ ላ ይ ተነ ስ ቶ ወደ ማታጠቢያ ቤት ሄ ደ።
የ ሻ ወር ቤቱን በር ዘ ግቶ ውሀ ውን እ ስ ከሚጨፈ ሻ ውከፈተና መልቀስ ጀመረ ። እ ን ባ ውብሶ ቱን
ሲያ በር ድለ ት እ ጆቹን ገ ላ ውላ ይ እ ያ ር ማሰ ማሰ ገ ላ ውን አ ሽቶ ተለ ቀለ ቀና ወጣ፡ ብር ቱካ ና ማቀለ ም
ያ ለ ውፎጣአ ገ ል ድሞ ልብሱን ሊለ ብስ ወደ መኝ ታ ክ ፍላ ቸውሲሄ ድ አ ል ጋ ውላ ይ ኸሉድ አ ል ጋ ልብሱን
ከወገ ቧ በታች ብቻ ለ ብሳ ከላ ይ እ ን ደተራ ቆተች ፈገ ግ አ ለ ችለ ት። በስ ስ ት ተመለከ ታትና "የ ማትበላ
ወፍ!" አ ለ በልቡ። ተጠግቶ ሊገ ና ኛ ት ቢሞክ ር ምን እ ን ደሚፈ ጠር ያ ውቃል። እ ን ደውምሰ ሞኑ ን ከሷ ጋ ር
የ ሚያ ደር ገ ውግብግብ ስ ፖር ት ማስ ሎስ ለ ተሰ ማውከተገ ና ኙ በኋላ ክ ብደት እ ን ዳ ነ ሳ ሰ ውደህ ና ምግብ
መብላ ት ጀምሯል።
ፀ ሀ ይዋ ብታዘ ቀዝ ቅ ምሰ ሚር ማስ ጂድ ሜ ድ አ ል ፈለ ገ ም፡ ሰ ሞኑ ን በጥቅ ሉ ቤቱ ነ ውየ ሚሰ ግደው፡
ትቷት ሲወጣአ ን ድ ነ ገ ር የ ምትሆን እ የ መሰ ለ ውይሰ ቀ ቃል። ልብሱን ከለ ባ በሰ በኋላ ሰ ሞኑ ን ማስ ጂድ

እንደሚሄድ ስለምታውቅ አብራውለማስገድ ስለፈለገች ገላዋን ለማታጠብ ወደ ማታጠቢያ ቤት ገባች። እየ ታጠበች ሁሴን ዛሬ ያደረጋትን አስታወሰችና እንባ እንባ አላት። ከሁሴን ጋርምሆነ ከሰሚር ጋር ስትገናኝ ምንምአይነ ት የእርካታ ስሜት አይሰማትም፡ ሚህል ሚህል ላይ ግን ስሜቱ ገረፍ አድርጓት ያልፋል።
ታጥባ ማግሪብን በአንድነ ት ከሰገዱ በኋላ እራት ውጪሊጋብዛት ይዟት ወጣ፡ ኸሉድ ወደ ድሮው ነፃነ ቷ እንድትማለስለት ያልፀለየበት ቀን የለም፡ "አላህ ተጠይቆ እምቢ አያውቅም! ሰጥቶ አይነ ሳኝም፡ ጣፋጯን ኸሉዴን ይመልስልኛል!" እያለ ራሱን ያፅናናል።
***
ይቀጥላል

ግርዶ

ክፍል ዘጠኝ

.
ማክሰኞ ረፋድ ላይ ኢስሚኢል መኝታ ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ ከሀገር ውጪእና ውስጥ ካሉ ሰዎች የተላከለትን መልዕክት ስልኩ ላይ ያነ ባል። ከፊሉ ለትዳር ይጠይቀዋል። ከፊሉ ገንዘብ ካልላኩልህ እያለ ይማፀነ ዋል። ከፊሉ አድናቆቱን ይቸረዋል። የሰዎቹ ሁኔ ታ ኢስሚኢልን እጅግ የሚፈትን ነ ው፡ ጨዋ ልሁን ቢል እንኳ የሚቅዱለት አይመስልም፡ መልዕክቶቹን ማንበብ ሲሰለቸው ዩስራ ጋር ደወለ። ከዚህ ቀደምየ ተገናኛቻቸውሴቶች ጋር የ መደወል ልምድ አልነ በረውም፡ ስልካቸውን ብሎክ ማድረግ ነበር የ ሚቀናው፡ ዩስራ ስልክ አታነ ሳም፡ ከብዙ መደጋገምበኋላ ስልኩ ተነ ሳ።
"እ? ምን ቀረህ? ምን ፈለግክ?"
"ኧረ ዩሲ ሰላምታ ይቀድማል! እንዴት ነ ሽ?"
"ልዘጋውነ ው!"
"እሺ አትዝጊው! ይቅርታ ልጠይቅሽ ፈልጌ ነ ውየ ደወልኩት። በጣምይቅርታ!"
ዩስራ እንባዋና ሳቋ እየ ተሽቀዳደማት "ተውባ ክህ?! ይቅርታ የ ሚያ ብሰውይማስልሀል?"
"እና ምን ልቀጣ?"
"ህሊና ካለህ ይቅጣህ! መጀመሪያ ሰውሁን! ያኔ ይቅርታ ለማጠየ ቅ ትበቃለህ!"
"አካበድሽውእኮ በጣም!"
ንዴቷ ከፍ ሲል ተሰማትና "ኧረ? ..." ንግግሯን ሜጨረሱን ትታ ስልኩን ጆሮውላይ ዘጋችው።
ኢስሚኢል ዩስራን ድጋሚ ለማግደምየ ነ በረውእቅድ ፍፁምእንደማይሰምር ተረዳ። ስልኩን አውጥቶ የ ሰሞኑ መደበሪያውጋር ደወለ። ነ ይ ሲላት አቤት ፤ ሂጅ ሲላት ወዴት ነ ገር ነ ች። ሰላምእንኳ ሳይላት "ስሚቤት ነ ኝ ነ ይ!" አላት። እየ ተቅለሰለሰች "እሺ መጣሁ!" አለችው፡ ሴቶቹ የ ሚፈልገ ውን ካሟሉለት አንድ ቀን ያገ ባኝ ይሆናል በሚል አጉል ተስፋ ቢያገ ባቸውሊሰጡት የ ሚቹሉትን ቀድመው ያስረክቡትና ባዶ እጃቸውን ይቀራሉ። በጫቃ የ ግንብ ቤት የ ሚሰራ ይመስላቸዋል። በወንጀል ተንጠላጥሎ ማገረክማእንዴት ይሆናል? ትዳር እኮ ብሩክ ተቋምነ ው፡ በቅድስና እንጂ በውንብድና የ ሚገ ኝ አይደለም፡ ያውቃሉ ግን ይሳሳታሉ። እውቀታቸውእምነ ት አልባ ስለሆነ ከማሳሳት አያናጥባቸውም፡
*
ማክሰኞ ማታውን የዘቢባ እናት አየር ሚረፊያ ደረሱ። ወ/ሮ ጀሚላ ቀድመውያውቁ ስለነ በር ከዩሱፍ ጋር ሄደውተቀበሏቸው፡ ዩሱፍ ወደ አየር ሚረፊያውሲነ ዳ ማንን ለመቀበል እንደሆነ አያውቅም፡ ልክ ቦሌ ሲደርሱ ወ/ሮ ጀሚላ "ከንዚያዬን ነ ውየ ምንቀበለው!" አሉት። በጣምደነ ገጡ፡ "እንዴት በድንገ ት ልትመጣ ቻለች?" ግራ እየ ተጋባ እናቱን ጠየ ቃቸው፡
"አንተውነ ሀ! ልጇን አስረግዘህ ጭንቅ ውስጥ የ ጣልከኝ! እኔ ብቻዬን መጨነ ቅ ሰልችቶኛል። መጥታ የ ሚሆነ ውን ታድርግ ብዬ ነ ውየ ጠራኋት!" አሉ። ዩሱፍ የ ዋሹት ውሸት ፍፁምአሜሪካ ደርሶ ይህን ያክል ከባድ ነ ገር ይፈጠራል ብሎአላሰበምነ በር። አፉ እንደተለጎመ ወ/ሮ ከንዚያ ከኤርፖርቱ ወጡ፡ እንዴት ብሎ አይናቸውን እንደሚያይ ጨንቆት ተንቆራጠጠ፡ ሰላምታ ከሰጣቸውበኋላ ድጋሚ ላለመተያየት ሲል የ ወ/ሮ ከንዚያን ሻንጣዎች መኪናውላይ በመጫን ከአይናቸውሸሸ። ሁለቱ እናቶች እጅግ ተነ ፋፍቀዋል። የ መኪናውየ ኋላ ወንበር ላይ ተቀምጠውእየ ደጋገ ሙሰላምይባባላሉ።

ሁኔ ታቸውዩሱፍን እያሳቀውሚኪናውን አስነስቶ ወደ ቤታቸውማሽከርከር ጀመረ። ይኼክስተት ለዘቢባምድንገተኛ እንደሆነ ገብቶታል። በልቡፈጣሪ የወ/ሮ ከንዚያን ልብእንዲያራራውተማፀነ። ቤት ገብተውዘቢባ እናቷን ስታይ እጅግ ደነገጠች። ለወትሮውበስድስት ወር አንዴ ብትማጣነው። አሁን ግን ከሄደች ገና ሶስት ወር እንኳ በቅጡአልሞላትም። የማጣችበት ምክንያት ሲገባት የፈጠሩት ውሸት ዋጋ ማስከፈሉን ተረዳች። ናፍቆታቸውን ተቃቅፈውከተወጡብኋላ ወ/ሮ ከንዚያ ተጣጥበውአረፍ አሉ። ዘቢባ ወ/ሮ ጀሚላ ክፍላቸውመግባታቸውን ካረጋገጠች በኋላ ወደ ዩሱፍ ክፍል ሄደች።
"ስማነገ አለቀልን! ምንድነውየ ምንላቸው?"
ዩሱፍ በሚታ ማማጣቷ በእናቱ ዘንድ ሜልካምትርጉምእንደሜይኖረውስለሚያውቅ አንገቱን አውጥቶ አለሞኖራቸውን ካረጋገጠበኋላ "ምን እንላለን ያውሸይጣን አሳሳተን ነዋ!"
"በውሸቱ ልንቀጥል?"
"እና? እውነ ትከምናደርገውአይሻልም?"
በአይኖቿ "ይሻላል" የሜል ምልክት አሳይታውወደ ክፍሏ ሄደች።
ዩስራ የዘቢባ እና የዩሱፍ ድራማእየፈጠረውያለውቀውስ ከጅሚሮውአስግቷታል። የማጋባት ፍላጎታቸውን እስከ ሜጨረሻውየሚያሳካ አልማስል ስላላት ስለውጡቱ ግልፅ ምክል አላገኘችለትም። የራስ ሙተማምኗ በኢስሜኢል ድርጊት ምክንያት ሜውረዱ ደግሞበምትፈልገውሜልኩእንዳታግዛቸው ከልክሏታል።
ጠዋቱን ዩሱፍ ከማስጂድ ሲማለስ ዘቢባ እንደለሜደችውወተት አፍልታ አቀረበች። እናቷ ሳሎን ውስጥ ገብተውሲማለከቱ ዩሱፍ እና ዘቢባ ወተት እየጠጡነው። ከአጠገባቸውተቀምጠውከፔርሜዙ ወተቱን ቀድተውስኳሩን እያማስሉ በደንብ ተማለከቷቸውና "እናንተ ምን ጉድነውየ ሰሚሁት?" አሉ።
ዘቢባምዩሱፍምአንገታቸውን ሰብረውዝምአሉ። ወ/ሮ ከንዚያ ዝምታቸውሀፍረት የወለደውእንደሆነ አስበውንግግራቸውን ቀጠሉ። "እናንተ ምን ብትዋደዱ ያልተጋባ ሰውእንዲህ ሜድረግ እንደሌለበት እድሜልካችሁን በየኪታቡስትማሩ ነውያሳለፋችሁት። ምን ልሁን ብላችሁ ከዚህ ፀያፍ ነገር ላይ ወደቃችሁ?" ጥያቄ አለሜሆኑ ለሁለቱምግልፅ ነበር።
ዘቢባ እየተቅለሰለሰች "እማእንጋባ ስንል አልሰማአላችሁን። እኛ የተፈጠረውን ስለምናውቅ ቤተሰባችን እንዳይሰደብ ጉዳችንን እዚሁእናፍን ብለን ነው። ማሳሳታችን ጥፋት ቢሆንምሜልካሙ ካልተሜቻቸላት ነብስ በሜጥፎውለማዝዝ ወደ ኋላ አትልም፡" አለች።
ወ/ሮ ከንዚያ ትኩር ብለውካዩዋቸውበኋላ "ያውምን ይደረጋል የተጀሜረ ነገር ለሌላ ሰውጩፍስ ማለት ከባድነው። Anyhow የሚያገባሽ ልጅ ማን ውስሜኢድሪስ? Yeah እሱን ከኒካሁ በፊት አረጋግተን እንነግረዋለን። እርግዝናውግን ሜውረድ አለበት።" ሲሉ ሁለቱምድርቅ ብለውቀሩ።
ሀኪምቤት ከሄዱ ውሽ ታቸውሊታወቅ ሜሆኑን ተገነዘቡት።
"ኧረ ልጅ ማስወረድ ወንጀል ነው!" ዘቢባ ነበረች
ወ/ሮ ከንዚያ ሳቁና "ሳያገቡ ሜርገዝስ?" አሉ።
"ታዲያ አንዱ ወንጀል አይበቃንም? ደግሞለሷምጤፍ ጥሩ አይደለም!" ዩሱፍ እንደምንምውሸ ታቸውን ለሜካላከል ታገለ።
ወ/ሮ ጀሚላ በሜሀል ተቀላቀሏቸው። የወሬውሜ ሻ ስለገባቸው"በባህላችን ሰባት ዘር ተቆጥሮ ካልሆነ ጋብቻ አይፈቀድም። ቀባሪ ልታሳጡኝ ነውእንዴ!?" አሉ።
እርግዝናውሜፈጠሩን ሁለቱምእናቶች አጋነውአላዩትም። አንዳቸውአንዳቸውን ቢቆጡፀቡ የሜፈጠረውቤተሰቡ ውስጥ ሜሆኑን ስለተረዱት በእርጋታ ነገሩን ለሜፍታት እየሞከሩ ነው።
*
ቀናት በቀናት ሲተኩ የሰሚር ልብ ኸሉድ ሌላ ሰውሜውደዷን ማጠርጠር ጀምሯል። ሰኞ ማታውን ሰሚር መኝታ ክፍላቸውውስጥ እንደተጋደመከራሱ ጋር ሙግት ገጠሜ፡ "ምናልባት ከሁሴን ጋር ይሆን?" ብሎ ራሱን ይጠይቅና "ከኔ የተሻለ ሀብት እያለውከሱ ሜርጣኝ አሁን ምን ፈልጋ ወደሱ ትዞራለች? ኧረ አታደርገውም፡" ብሎ ለራሱ ምላሽ ይሰጣል። ኸሉድ እና ሁሴን ከተገናኙ እና ከቁጥጥሯ ውጪየ ሆነ ውነገር ከተከሰተ ዛሬ ሳምንቱ ነው። ሰሞኑን በእንቅልፍ ልቧ የሁሴንን ስምሜጥራቷ ዕረፍት ነስቶታል። "ኸሉዴ?" አለ አልጋውላይ ከረዥምትግልና ልፊያ በኋላ የተዘረረችውን ሚስቱን እያየ።
"ሰሜሬ ውዴ!" በገዳይ ሳቋ ጉንጮቿን አሰርጉዳ አይኖቿን አስለማለ ቻቸው።
ልቡ ውስጥ ፍቅሯ በጥልቅ ተከትቧል። በስስት ነውየሚያያት። "ስራ ሜጀሜር ያልነውን ተውሽው እንዴ?"

"አዎ ባክህ ጥሩ ስሜቱ ላይ ስላልሆንኩ ቢቀርብኝ ይሻላል!" የሜኖቅ ስሜቷ ያስቀባጠራትን ሁሉ ረስታዋለች።
"እና ቤት መዋሉ ከደበረሽ ለምን ዘቢባ ጋ አትሄጂም?"
"አትጨቅጨቅ ከደበረኝ እሄዳለሁ።" ብላ ጉንጩን ስትስመውስልኳ ጠራ። ስልኳ በእሱ በኩል ስለነበር አንስቶ አቀበላት። የማታውቀውቁጥር ስለነበር አነሳችው።
"ሄሎየኔ ጣፉጭ ከወዲያ የተሰማውየጎረምሳ ድምፅ ነበር። ስልኩ ስፒከር ላይ ባይሆንምሰሚር በደንብእየተሰማውነ ው።
"ምን? ማን ልበል?" ደንግጣለች።
"ባለፈውውብ ፍቅር የሰጡሁሽ አገልጋይሽ ነኝ ንግስቴ" ንግግሩ በሳቅ እና ቀልድ የተዋዛ ነው።
"አልገባኝምማን ልበል ይቅርታ!" የሰሚር ፊት መቅያየርን ስትማለከት የምትገባበት ጠፍቷት የጠየቀችውጥያቄ ነበር።
"ሁሴን ነኝ። ምነ ውጠፉሽ? ቤት ብቅ አትይም?"
ድንጋጤዋ ሁሉ ጠፍቶ ቅዝቅዝ እያለች "እሺ እመጣለሁ!" አለች። ሜልሷ ለሰሚር እጅግ የሚያስደነግጥ ነበር። ከምሽቱ ሶስት ሰዓት አልፏል።
"በቃ አሁን እንኳ ማሽቷል። ነገ ብቅ በይ!"
"እሺ!"
ስልኩ ሲዘጋ ሰሚር ወደ ኹሉድ እያፈጠጠ"ማ ውን?" አላት። "አትጨቃጨቅ! ልተኛበት!" ብላ ተሸፋፍና ተኛች። ሰሚር ለሊቱን እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር እንዲሁ ሲገላበጥ አደረ።
ጠዋቱን የንጋት ስግደት ለማስገድ ቀደምብሎ ተነሳና ገላውን ታጠበ። ከሻወር ሲወጣ ኹሉድ ከነእርጥበቱ እቅፍ አደረገችውና ፎጣውን ገፋውሻወር ልትወስድ ገባች። ሰግደውሲጨርሱ ማታ የደወለላት ማን እንደነበረ ለማዋት ከስልኳ ላይ ስልኩን ወሰደ።
ከኋላውማስገጃ ላይ ተቀምጣየምትዘክረውን ሚስቱን እያየ "ኹሉዴ ቆይ ግን ማ ውማታ የደወለልሽ?" አላት።
"የማላውቀውቁጥር ነ ውባክህ!" አለች።
የማታውናየአሁኑ ሜልሷ ማካከል ልዩነት መኖሩን ከተማለከተ በኋላ ዝምታን ሚረጡ፡ "ምናልባት የማታውቁጣዋ ምንጨማጠር ጠሬ ይሆናል" ሲል ራሱን ገሰፀ።
ቁርስ ከበሉ በኋላ ልቡ ትቷት ሜዱን እጅግ ቢፈራምአሜራጭስላልነበረውብቻዋን ትቷት ወደ ስራው ሄደ። ይህን ወር በኹሉድ ምክንያት ሆስፒታል አድሮ አያውቅም። ባልደረባዎቹ ስለተረዱት በቻሉት ማጠን የሱን ተራ እየተተካኩ ይሸፍኑለታል። ቀኑን ለመቅረት ፍፁምየማይችለውበዚህ ምክንያት ነ ው።
ሰሚር ከቤቱ ከወጣከአንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ሁሴን ስልክ ደወለ። ስልኩን ስታነሳው"እሺ የኔ ውድ እየመጣሽ ነ ውን?" አለ።
ቁጥሩን በደንብለማዋት እየሞከረች "ማ ህ? አላወቅኩህም!" አለች።
"ሁሴን ነኝ! አሁን ቤት ነ ይ!"
"ኧ? ምን? እ እ እሺ መጣሁ" ድምጿ እምቢ ከማለት ተነ ስቶ እሺ በማለት ተጠናቀቀ። ልብሷን ለባብሳ ሁሴን ቤት ሄደች። ገ ብተውትንሽ ከተጨዋወቱ በኋላ ሁሴን ስሜቱን አስታገሰባት። ከሱ ጋር ግንኙነት ስትፈፅምከሰሚር ጋር የምታደርገውየአትንካኝ ትግል ፍፁምየለም፡ እንዳደረጋት ትሆናለች።
እቅፉ ውስጥ ራሷን ስታገኘውማን እንዳመጣት ግራ ግብት አላት። ራሷን ከቤቷ በአንዴ ሁሴን ቤት ውስጥ በምን ሜልኩ እንዳገኘችውለእሷምግልፅ አይደለም፡ ሁሴን በደንብአቅፏት ከንፈሯን ማጣም ጀሚረ። ቅፍፍ አላት። በእጇ ገፍታ ከላይዋ ላይ አስነሳችው። ረጋ ብሎ ልብሷን አቀበላትና ለባብሳ ስትወጣ ሊሸኛት ተከተላት። እንባዋን መቆጣጠር እየከበዳት ትታውበእግሯ ሜድ ስትጀምር እሱ በሚኪናውእየተከተለ ለመና ት። የሰውአይን እያረፈባት መሆኑ ሲገባት ከእይታ ለማምለጥ ስትል ሚኪናውውስጥ ገባች። ብሎካቸውድረስ አደረሳትና የታሸገ አስር ሺህ ብር ቦርሳዋ ውስጥ ከተተላት።
እምቢ ስትለውየሚጠረውግርግር ጎረቤቶቿ አይን ውስጥ እንዳይከታት ስለፈራች ቦርሳዋን ይዛ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ወዳለውቤቷ ተራመደች። እንባዋ መንታ መንታ እየሆነ ከአይኖቿ መፍሰስ ጀሚረ።
ቤት ገብታ ገላዋን እየታጠበች አነ ባች። ራሷን እንኳ የማታዝ መሆኗ ከህይወት ተስፋ አስቆረጣት።
"ሁሴን ድግምት አሰርቶብኛል!" አለች ለራሷ። ታጥባ ስትጨርስ የድግምት የቁርዓን ህክምና የሚደረግበትን የቴሌቭዥን ቻናል ፈለገች ልክ ስትከፍተውአንድ ጢም ያሉ ሰውህክምናውን

ያነበንባሉ "ማጂዕቱምቢሂ ሲህሩ ኢነ ሏሀ ሰዩብጢሉህ!" ሲሉ ተንደርድራ ሶኬቱን ነቀለችውና ሜዴቱ ላይ ተዘረጋች። ትንሽ ደቂቃ ቆይታ ስትነቃ የሳሎኑ መሀል ላይ ማዝረጋቷ ገርሟት ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ፈተናውእጅግ ከብዷታል። ፈጣሪ ምንምባሮቹን ከጤና ፣ ከገንዘብእና ከልጆች በማጉደል እንደሚፈትን ብታውቅም"የኔስ በዛ! ራሴ ላይ ሙብት አጣሁ! የኔ እጅግ በዛ!" ብላ አሚረችና ማታገስ እንዳለባት ስታስብ"ይቅር በለኝ ጌታዬ!" ብላ በመሚሯ ተፀፀተች።
ችግሯን ለሰሚር በግልፅ ነግራውመፍትሄ ሚፈለግ እንዳለባቸውአማ ች። ያለሰሚር እገዛ ካለችበት አዘቅት መውጣት እጅግ ከባድነ ው። ማታ ሲመጣየ መጀመሪያ ስራዋን ለሰሚር ድግምት እንደተሰራባትና የቁርዓን ህክምና እንደሚያስፈልጋት ማሳወቅ እንዲሆን አሰበች።
***
ይቀጥላል ...

ግርዶ

ክፍል አስር (10)

.
ዩስራ የኢስሚኢል ንቀት እጅጉን ውስጧን ቢጎዳውምሌሎች ሰዎች በእሱእንዳይጎዱእና እሱም እንዲስተካከል መፍትሄ የሚፈልጉ ሰዎች ባሉበት ለመፍትሄ እያሰበች። "ባዋርደውየእውቅና ካባውን ለመግፈፍ የምጥር እንጂ ማንምእውነ ት ያለኝ አይመስለውም! ደግሞምእሱንምከጥፋት አያርመውም! ስለዚህ ጌታዬ እንዲያስተካክለውእፀልያለሁ!" ብላ ለልቧ ያረከሳትን ማንነ ት በፀሎት ማንፃት እንዳሰበች ነገረችው። ኢስሚኢልን በልቧ ይቅር ስትለውሀዘኗ ጉልበት አጣማስል ተለያት። "ጌታዬ ሆይ ድንበር አላፊውን ባሪያህን ማሳሰቱን ግለጥለት! ልቡን በሚልካምነ ገር ላይ አፅናለት።" የሁል ጊዜ ዱዓዋ ሆኗል።
ዩስራ ቤት ውስጥ ከዘቢባ እናት ጋር ተቀምጣእየተጨዋወቱ ሳለ ስልኳ ጠራ። ኢዘዲን ነበር። ኢዘዲን መሻሺድነ ው። አደዋወሉ ከሚድረክ ዝግጅቶች ላይ መጥፋቷ አሳስቦት ነበር።
"ዩስራ እንዴት ነሽ?"
"አለሁ ኢዜ ሁሉ አማን?"
"አለሁ ምን ውጠፋሽ? ሁለት ዝግጅቶች ላይ ሳጣሽ እኮ በሰላምአልመሰል አለኝ!"
ዩስራ ምን ማለት እንዳለባት አታውቅም። ለኢዘዲን ኢስሚኢል ያደረጋትን ነገረችውማለት ትልቅ ቀውስ በሁለቱ ማካከል ተፈጠረ ማለት ነ ው። ኢዘዲን በእምነ ት ስምሚዘረክረክ በጣምነ ውየ ሚጠላው! ብዙ ጊዜ ከወንዶች ጋር ረዘምላለ ሰዓት ቆማስታወራ አግኝቷት "ወሬ ቀንሺ! ንግግርሽን ሳይሆን ሴትነ ትሽን እያዳማጡእንዳይሆን!" ብሎ ተቆጥቷታል። ምን ብላ እንደምትሚልስለት ተቸግራ "ትንሽ እረፍት ፈልጌ ነ ው!" አለችው።
"እረፍት ጥሩ ነ ው። ግን አደራ ከማስሚር እንዳትወጪ ከዚህ ብትርቂ እንኳ የተሻለ እንጂ የዘቀጠቦታ እንዳላይሽ!"
ዩስራ የኢዘዲን ወንድሚዊ ምክር እና ስስት እየገረማት በልቧ "አሁን ኢስሚኢልን ምኢዘዲንን ምእኩል መሻሺድ እንላለን?" አለችና "እረ አብሽር ምንምአትስጋ ባይሆን በዱዓህ አትርሳኝ!" ብላው ተሰነ ባበቱና ስልኩ ተዘጋ።
የኢስሚኢል ድርጊት ነሺዳ የተባለ ሁሉ እንዲያቅራት ቢያደርግምበእንክርዳዱ ምክንያት ስንዴውን መድፋት አግባብ አለመሆኑ ታሰባት። እንክርዳዶቹ ጥቂት ናቸው። በእነ ዚህ እንክርዳዶች ምክንያት ቀን ከሌት ለህዝቡ ሲለፉና ሲደክሙየ ሚውሉ ስንዴዎችን በጅምላ ሚፈረጅ ጤነ ኝነ ት አለመሆኑን አማ ች። ከብዙ ፈተና አምልጠውለጌታቸውየ ታመኑ እልፍ መሻሺዶች ፣ ሰባኪዎች እና ፀሀፊዎችን በኢስሚኢል ምክንያት ልትጠላቸውእንደሚይገባ የኢዘዲን ንፅህና አስታወሳት። "በነ ጥብ ጥላቻ ምክንያትማእልፍ ፍቅርን አልገፋም!" ለልቧ ነገረችው። ለነ ገሩ የብዙዎች ችግር ነገሮችን ሁሉ በአንድ ቅርጫት የማከተት አባዜ ነ ው። አንድ መሻሺድ ሲያጠፉ እልፍ ጨዋዎቹን አብሮ መኮነ ን!
የፈጣሪ ቃል "ማንምየ ምንንምሀጢዓት አይሸከምም!" እንደሚል ተዘንግቷል። ዩስራ ራሷን ገሰፀች።
.
የዘቢባ እናት ከማጡሳምንት ሊሞላቸውተቃርቧል። እስካሁን ድረስ በጋብቻውዙሪያ ከአንዴ በቀር ከነ ዘቢባ ጋር አላወሩም። ከወ/ሮ ጀሚላ ጋር ግን ብዙ የማከሩበት ይመስላል። ኢድሪስን በተፈጠረው

ነገር ዙሪያ ለማማከር ቀጠሮ ለእሁድ ቆርጠዋል። ምሳ ከማብላቱ በፊት የዝሁር ሰላት ሴቶቹ በአንድነት ሊሰግዱ ከስግደት በፊት የሚደረገውን ትጥበት አድርገው ሲማላሱ ዩስራ እና ዘቢባ ወደ ኋላ ቀሩ።
"ምነው ስገዱእንጂ!" ወ/ሮ ከንዚያ ነበሩ
ዩስራ ፈገግ ብላ "ሰላት የለኝም" አለች። የወርአበባ ላይነኝ ለማለት አቋራጭመንገድ ማጠቀሟ ነበር።
ወ/ሮ ጀሚላ ወደ ዘቢባ ዞረው"አንቺስ?" ሲሏት "እኔ ምየለኝም" አለች። ዩስራ ቆንጠጥአደረገቻት። እርጉዝነኝ ተብሎየ ወር አበባ እንደሚይኖር ዘቢባ ዘንግታዋለች። ወ/ሮ ከንዚያ እና ወ/ሮ ጀሚላ ብዙምትኩረት ሳይሰጡት ወደ ስግደታቸውገቡ። እነሱ ሲሰግዱ ዩስራና ዘቢባ ሹልክ ብለውወጡ።
"ምን እንዳልሽ ግን ታውቂሻል?" ዩስራ ተበሳጨች
"አላሰብኩትምነበር ግን እነሱምየባነኑ አልመሰለኝም"
"ባክሽ ሲሰግዱ በደንብነውየሚሰላስሉት! ማማላጨፈልጊ!"
ዘቢባ ምንምአይነት ማማላጨአልመጣልሽ አላት። ሰግደውሲጨርሱ ምሳ ቀረበ። በልተውእንደጨረሱ ወ/ሮ ጀሚላ "ተነሱእስኪ እዚህ ደረስ ብለን እንመጣለን!" አሉ። ወ/ሮ ከንዚያ ግራ ሲጋቡ ወ/ሮ ጀሚላ "እዚህቹ ቅርብናት!" አሉ።
ዘቢባ ቤት ውስጥየምትቆመዋን ራቭ ሚኪና አስነሳች። የተገዛውለሷ ቢሆንምሁሌምከዩሱፍ ጋር ስለምትንቀሳቀስ ብዙ ጊዜ አትነዳም፡ ዩሱፍ ሚኪናዋ እንዳትዝግ ብሎአንዳንዴየራሱን ሚኪና እያሳረፈ ባይነዳት እስካሁን ተበላሽታነበር። ከቤት እንደወጡዘቢባ "ወዴት ነን ግን? ሚኪናዋ ብዙ ነዳጅ ያላት አይመስለኝም" አለች። ወ/ሮ ጀሚላ ነዳጅ መንገድ ላይ እንድትሞላ አዘዟት። ሰሞኑን ሚኪናዋን በደንብ ማጠቀማቸውስለማይቀር ብለውይማስላል። ነዳጅ ሚደያ አግኝተውነዳጅ ከሞሉ በኋላ ወደ አንድ ታዋቂ ሆስፒታል እንድትነዳውጠቆሟት። ወደ ሆስፒታሉ ደርሰውከሚኪናው እንደወረዱ ወ/ሮ ጀሚላ የማጠብትን አላማአጠር አድርገውተናገሩ። ዘቢባን እያዩ "አሁን የእርግዝና ምርመራ ታደርጊያለሽ።" አሉ። ዩስራ እና ዘቢባ ማሻነፋቸውን ተረዱ። ዘቢባ ውስጥ ከገባች ወጪከማውጣት በዘለለ የሚያተርፉት ነገር ስለሌለ እውነቱን ለመናገር ወሰነች።
"ዩሱፍ አልነካኝም" ዘቢባ እውነቱን አፈረጠችው።
ሁለቱ ወይዘሮዎች ትልቅ ሽክምየቀለለላቸውያህል ተነፈሱ። ወ/ሮ ጀሚላ እየሳቁ "ለሌላ ጊዜ ያረገዘች ሴት የወር አበባ አታይምእሺ!" አሏት። በምን እንደጠረጠሩ ገባት። ውስጧተስፋ የሚቁረጥ ስሜት ነገሰ። የልጅነት ፍቅሯን እስከ ሚጨረሻውልታጣውእንደሆነ ተሰማት። ለማጥፋት እንኳን በማይመች ሜልኩ ወጥረውይዘዋታል። ለሷየምድር ህይወት ያለ ዩሱፍ ማለት ቀን ያለፀሀይ እንደማለት ነው። ኢድሪስ እጅግ አስጠላት። አባት ቢኖራት ተመኘች። "አባቴ ኖሮ እያለቀስኩ ብነግረውለኔ ሲል ከባህሉ ጋር ለማፋጥአይፈራም" ስትል አሰበች። አሁን በቀረውአንድ ወር ከሳምንት ጊዜ ውስጥምን ምክንያት ፈጥረውማማላጥ እንደሚችሉ ከዩሱፍ ጋር መማከር አለባቸው። ሁሉንምአኩርፋ ሚኪናው ውስጥገብታ አስነሳቻቸው። ተከትለዋት ገቡ። ሳታናግራቸውሚኪናውን ወደ ቤት ነዳቻቸው። አሁን እስከዛሬ ተሰምቷት የማያውቅ ከባድ ፍርሀት ይሰማት ጀምሯል። ዩሱፍን የማጣት! የልጅነት ትዝታዋን የማጣት ፍርሀት።
***
ሰሚር ቤት ከመግባቱ ኹሉድ ልትነግረውያሰበችውን የድግምቱን ዜና ልታበስረውተዘገጃጀች። ፊቱ ትክክል አይደለም፡ እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ።
"ሰላምዋልክ ውዴ?" ኹሉድ ሁኔ ታውአስደንግጧታል። ልታቅፈውስትቀርብ ገፍትሯት ወደ መኝታ ክፍል ገባ። ተከተለችው። "ምን ውምን ሆንክብኝ?" ቅላፄዋ ውስጥስቃይ አለ።
"ሸርሙጣእንዳገባሁ ሳውቅ አመመኝ! ባሏ ከቤት እግሩ ሲወጣበገንዘብ ተገዝታ ከማንምጋር የምትሸረሙጥ ሚስት እንዳለኝ ሳውቅ ቀፈፈኝ!!" ንዴቱን ለመቆጣጠር አልጋውላይ ተጋደመ፡ ከቆመ እንዳይመታት ሰግቷል።
"እንደምታስበውአይደለም"
"ምኑን ነውየማስበው?" አለና ተነስቶ ቦርሳዋ ውስጥየነበረውን ሁሉ አልጋውላይ ዘረገፈው። ሁለቱ እስር አስር ሺህ ብሮች ከአልጋውላይ ወደቁ።
"ይኼን ብር የሰጠሽ ሰውሁሉንምነገረኝ! ምን አጎደልኩብሽ እኔ? ሻርሞጥየሚያስመኝ ምን አጎደልኩብሽ ንገሪኛ!" ፊቷን በጥፊ ደረገማት። በውስጡፊቷን በመምታቱ እየተፀፀተ አልጋውላይ

ጋደምብሎ ራሱን ለሚጋጋት ሞከረ።
ከኹሉድ አይኖች እንባ ያለማቋረጥ ፈሰሰ። ተንሰቀሰቀች። የውስጧህ ማምሰይበቃት በጥፊ መሙታቷ አበገናት።
"እኔ እኮ ሚታ ልገናኝሽ ስሞክር እማኪ ስትይ ፤ ስታስቸግሪኝ አለማጥርጠሬ? ለካ አንቺ ቀኑን አለማሽን ስትቀጪነ ውየ ምትውይው! ወይኔ ሰሚር!" ብግን አለ።
ከቆየ ቸግር እንደሚፈጠርና ከዚህ በላይ ቀውስ ውስጥእንደሚ ባ ስለገባውተነ ስቶ ወደ ዓደኛውቤት ሄደ። ኹሉድ ተንሰቀሰቀች። ህይወትሽን አጥፊ አጥፊ አላት። ማታጠቢያ ቤት የነ በረውን የሲንክ ማፅጃ አሲድ ለሜጨልጥ ወደ ማታጠቢያ ቤቱ ተጣደፈች። በሩ ላይ ደርሳ የአሲዱን ማዣዣአነ ስተኛ ጀሪካን ስትከፍተውስልኳ ጠራ። አየችው፡ ቁጥሩን አታውቀውም፡ አነ ሳችው፡
"የኔ ውብእንዴት ነ ሽ? ሁሴን ነ ኝ!" የአሲዱን ማዣዣ ወደ በታውማላሰችው፡
"አቤት?"
"ባልሽ ዛሬ ደውሎ ስለፍቅራችን ብዙ አወራኝ። ተቆጣሽ እንዴ?"
"አዎ!"
"በቃ አይዞሽ እኔ ቤት መኖር ትችያለሽ እሺ!"
"እሺ!"
ስልኩ ሲዘጋ ሄዳ አልጋዋ ላይ ተዘረረች። ውስጧን ለሁሴን ባሪያ እንድትሆን የሚያደርግ መጥፎ መንፈስ ተቆጣጥሮታል።
.
ሰሚር ከቤት እንደወጣበቀጥታ ያሜራውወደ ዩሱፍ ጋር ነ በር። ቤታቸውአቅራቢያ ሲደርስ የሀሚኒ ፀሀይ አቆልቁላ ስለነ በር እነ ዩሱፍ ሰፈር ያለውማስጂድ እየሄደ ደወለለት። ማስጂድ ለማ ናኘት ተቀጣጥረ ውከሰገዱበኋላ ተገናኙ። ዩሱፍምሰሙኑን ከዘቢባ ጋር በተያያዘ የገባበትን አጣብቂኝ ሊያጨውተውዓጉቷል። የሰሚርን ፊት ሲማለከተውግን የሚያወቀውሰሚር አልማስልህ አለው፡ በጣም ቀልቷል። ሰፈራቸውያለ አንድ ካፌእንደተቀማጡዩሱፍ "ምን ተፈጠረ?" ሲል ጠየቀው፡ ሰሚር እንባ እንባ እያለውየ ኹሉድን ከጀርባውሽፍጥ ማስራት አረዳው፡ ዩሱፍ እጅግ አዘነ ። ግን ደግሞኹሉድ እንዲህ ታደርጋለች ብሎ ማመን ከበደው፡
"ግን እርግጡኛ ነ ህ?" ዩሱፍ ለሚጋገ ጥየ ሰደዳት ጥያቄ ነ በረች። ሰሚር ከስልኩ ላይ የተላከለትን ፎቶ አሳየ ው፡ ማመን አቃተው፡ ሁሴን እና ኹሉድ አልጋ ላይ ተኝተውተቃቅፈውየ ሚያሳይ ምስል ነ በር።
"ማን ላከልህ?" ዩሱፍ በድንጋጤአፉን በእጁ ሸፈነ ።
"ሁሴን ተብዬውን ደውዬ ሳወራውባል እንዳላትእንደሚያውቅ እና ፍቅረኛውእንደሆነ ች ቀባጠረልኝ። አላምን ስለውላከልኝ!"
ዩሱፍ ኹሉድ ለምን ይሄን እንዳደረገ ች ማወቅ ስለፈለገ "እስኪ እኔ አናግራታለሁ እሷ ዛሬ እኛ ጋር ትደር። አንተ ቤት ትገ ባለህ። " ብሎ ከዘቢባ ጋር ለሜድ በማስብ ወደ ዘቢባ ደውሎነ ገ ራት። ነ ገ ር ግን ዘቢባ ሰሙን የቁምእስረኛ ስለሆነ ች እንድትወጣአልፈቀድ አሏት። ዩስራ ጋር ደውሎ ከሷ ጋር ሄደ።
ዩሱፍናዩስራ እነ ኹሉድ ቤት ሲደርሱ ኹሉድ ተኝታ እያለቀሰች ነ በር። ለማተኛት ሞክራ አልተሳካላትም፡ ሲያንኳኩሰሚር ይሆናል አስረዳዋለሁ በሚል ጉጉት ተንገ ብግባ በሩን ከፈተችው፡ ዩስራ እና ዩሱፍን ስትማለከት ረጋ አለች። ቤት ውስጥ ገ ብተውሲቀማጡየ ሚገ ላ ለማቀራረብ ተንጎ ዳጎ ደች። ዩሱፍ ተቀምጠውየ ማጠብትን ጉዳይ ብቻ እንዲያወሩ ሲጠይቃት ሜጅሊሱ ላይ ተቀምጣ ጥያቄውን ማስ ማት ጀሚ ች።
"ያውከሰሜ ጋር የተፈጠረውን ሰምተነ ዋል። ዛሬ አንቺ እኛ ቤት አድረሽ እንማከርበትና ችግሩን እንፈታለን። " ብሎ በአጭሩ የ ማጠብትን ጉዳይ አስረዳት።
ያለምንም ማንገ ራገ ር ተስማማች። ዩሱፍ ሰሚርን ማስ መ እንደሜቻል ታውቃለች። ሁሉንምለእሱ ብትነ ግረውጭፍትሔእንደሚያረ ውምአምናለች። በሩን ቆላልፈውይዘዋት ወደ ቤታቸውሄዱ። ሰሚር ንዴቱ ስላልበረደለትና ብቻውን ቤት ሜደሩ አልጥምስላለውወደ ቤተሰቦቹ ቤት ሄደ።
ማታውን ዩሱፍ ፣ ዘቢባ እና ዩስራ ኹሉድን ከበውየ ተፈጠረውን ጉድ ሁሉ ሲሰሙአ ማሹ።
የ ምታደርገ ውን እንደማታውቅና ድግምት እንደተሰራባት ሲሰሙሁለቱ ሴቶች ወደ ውጪዩ ሱፍ ደግሞወደ ውስጥአለቀሱ። ዩሱፍ ባለመግባባት ምክንያት ሊፈርስ የነ በረውን ትዳር አስቦ እጅግ ተቆጨ፡ "ስንት

ትዳር እንዲህ ባለ የሚታይ እጅ ፈርሶ ይሆን?" ራሱን ጠየቀ። በነጋታውሰሚርን አግኝቶ የተፈጠረውን ነገር በግልፅ ለማስረዳት ወሰነ ።
ወ/ሮ ጀሚላ ዩሱፍ እና ዘቢባ ከኸሉድ ጋር አወርተውሲጨርሱ ከምሽቱ አራት ሰዓት ገደማላይ ልብ የሚየሸብር ዜና አረዷቸው፡ የኢድሪስና የዘቢባ ኒካህ ከሁለት ቀን በኋላ በአስቸኳይ እንዲደረግ ከኢድሪስ ቤተሰቦች ጋር ተስማምተዋል። ከዚህ በላይ ከባድ ሚዶ በሁለቱ ህይወት ውስጥ የለም፡ ዩሱፍ እስከአሁን በግልፅ ያልታየ ውዘቢባን የማ ጠቅ ፍርሀት እጅግ አሸበረው፡ የእናቱን ቃል ማጣስ በፍፁምአይታሰብም፡ ፈጣሪ መውጫቀዳዳ አያሳጣንምበሚል ተስፋ ለሊቱን ተኝቶ ለማደር ቢሞክርምአልተሳካለትም፡ አይኑ በአግባቡ ሳትጨፈን የጁምዋ ለሊት ፈጀረች። ሰማይዋ ጠራች፡ ማጻዚኑምወደ ማስጂድ ተጣራ።
ንጋቱን ዘቢባ ዩሱፍ ወደ ማስጂድ ሲወጣየ ዉጭውበር ጋር ቆማጠበቀችው፡ "ምን ትሰሪያለሽ ብርድ ላይ?" በስስት እያያት አንሾካሾከ።
"ምን ወሰንክ? ሁለት ቀን ብቻነ ውያለን! ሁለት ቀን! እንዳትዘገይ! ካረፈድክ እንቀደማለን!" ለቅሶዋ ድምጿን በሳግ እያጠረውበሹክሹክታ ለማ ችው፡
"ምን እናድርግ የኔ ውድ? አንቺን አጥቼ መኖር አልችልም!"
"ይዘኸኝ ጥፋ! ለሁለት ወር እንጥፋ! ኒካህ እሰርልኝና ላርግዝልህ ያኔ ይቀበሉናል!"
"የእነ ሱእርግማን እየ ወረደብን ምኑን ኖርነ ው?" ዩሱፍ እናቱን ፍፁምማስከፋት አይሻም፡
"እና እኔ ያንን ሰዉዬ ላግባ!? አትወደኝምእንዴ? ኸረ እባክህ ፍርሀትህን ተው! እቴቴ ለሁለት ወር ያላንተ መኖር አይከብዳቸውም፡ እኔ ላይ ህይወቴን ሙሉ አንተን የማጣት ፍርድ አትፍረድ!"
እየ ተንሰቀሰቀች ሳታስበውድምጿ ከፍ አለ።
"እወድሻለሁ ዘቢባዬ! ከማንምከምንምበላይ ውድነ ሽ። ግድየ ለሽምእኔ ሙሉ እፈልጋለሁ አትጨ ቂ!" ብሎ አቅፎ ሲያባብላትና እሷ ስትንሰቀሰቅ ወ/ሮ ጀሚላ ከቤት ወጡ፡
"ነ ይ ግቢ አንቺ!" ቁጣቸውፊታቸውላይ ይንቀለቀላል። ከእቅፉ ወጥታ እየ ተንሰቀሰቀች ወደ ክፍሏ ሄደች። ዩሱፍ የተዘበራረቀ ስሜቱ ውስጥ እየ ዋለለ ወደ ማስጂድ ሄደ። ጌታውሙሉ እንደሚየሳጣው አምኗል።
***
ይቀጥላል ...

ግርዶ

ክፍል አስራአንድ (11)

.
ሰሚር ኸሉድ በዚህ ሚሊኩ ከሌላ ወንድ ጋር ከጀርባውትባልጋለች ብሎ አስቦ አያውቅም፡ እያንዳንዷ እምቢታዋን እና ልዩ ፀባይዎቿን ከክስተቱ ጋር ገ ሚደው፡ "ለካ ልቧ ወደሱ ተዘንብሎነ ውእንዲህ ሚጫወቻ ያደረገ ችኝ!" ተሚረ። በዚህ መነፈስ ስራ መግባት ስለከበደውአስፈቅዶ ተመለሰ። ብቻውን ከሆነ ብስጩቱ እንደሚ ድለውስላሰበ ቀኑን ከዩሱፍ ጋር ለማሳለፍ ወደ ዩሱፍ ቢሮ ሄደ። ዩሱፍ ትልቁ ሱቅ ውስጥ ያለውቢሮውውስጥበሩን ቆልፎ ዘቢባን ማቹረፊያ ዘዴእያፈላለገ ነበር። ፀሀፊው ደውላ የሰሚርን መምጣት ስትነ ግረውበሩን ከፈተለት። ሁለቱምልብ ውስጥ የማጣት ስጋት አለ።
የደከመሰላምታ ከተለዋወጡበኋላ ሰሚር በረዥሙተነ ፈሰና "ኸሉዴን ለመፍታት አስቤያለሁ!" አለ።
ዩሱፍ የታችኛውን ከንፈሩን ወደ ፊት እየ ለጠጠ ያወራውወሬ ተራ ሚሆኑን ሊገልፅለት ሞከረ። ሰሚር ቀጠለ "ከዚህ በላይ ሚታገስ አልችልም፡ እፈ..." ዩሱፍ አላስጨረሰውም፡ "በቃ! ሲሆን ፀባይዋ ሲቀየር ጠርጥረህ ህክምና መውሰድነ በረብህ! ራሷን ለማጥፋት ስትሞክር ፤ ፀባይዋ የሁለት ሰውሲሆንብህ እንኳ ውስጧን ሌላ አካል እያዘዘውሚሆኑን አትጠረጥርም?"
ሰሚር ስለ ሁሴን የሚየወራ ማስሎት "እኔ እኮ በጣምነ በር የማሚት እንዴት ልጠርጥራት?" አለ።
ዩሱፍ ዘቢባን የማጣት እልኸን ሰሚር ላይ የሚወጣይመስል እየ ጮኸበት "አይገ ባህምእንዴ? ልጅቷ ድግምት ተሰርቶባታል። ልጁ ጋር እንደሄደች የምታውቀውራሱ ሁሉምነ ገር ካለቀ በኋላ ነ በር! እንዴት የአንድ ሚስትህ ፀባይዋ ሲቀየር ምክንያቱን ሚደዳት ይቸግርሀል? ቀሽምነ ህ!"
ሰሚር ዩሱፍ የሚለውን ሁሉ ማመን ቸገ ረው፡ የእስከዛሬ ፀባይዋን እንደገና በአዲስ ሚ ፅር ቃኘው፡

ፀባይዋ ሲቀየር ፣ ስትሰድበው፣ አካሏን አላስነካምስትል ደግሞሜሳ ምንምእንዳልተፈጠረ ስትሆን! ሁሉምግልፅ ሆኖ ታየው። በእጁየላይኛውመዳፍ ግንባሩን እየመታ "ቀሽምነኝ!" አለ።
"አዎ ቀሽምትህ ግልፅ ነው። ይልቅ የቁርዓን ህክምና መጀመር ስላለባት ይቅርታ ጠይቃትና ይዘሀት ሂድ!" ዛሬ ዩሱፍ ንግግሩ ሁሉ ቁጣሆኗል።
የሰሚርን ጉዳይ አውርተውሲጨርሱ በዘቢባ እና ኢድሪስ ዙሪያ መከሩ። ምንምአይነት ሀሳብ ለጊዜው ብልጭአላለላቸውም። መጨረሻ ላይ ሰሚር "ለምን ኢድሪስን ጋብቻውን እንዲተውአትጠይቀውም?" ብሎ ትግሉ ከኢድሪስ ጋር የሚሆንበትን አዲስ እቅድ አመላከተ። ዩሱፍ ለጊዜውኢድሪስን ከማናገር ውጪ ሌላ ምንምአይነት አማራጭአልነበረውም። "ፍቅሬን ተውልኝ!" ብሎ ሊማፀነው፤ ዝቅ ብሎ ሊለማመጠው ሆነ ። ለዘቢባ ሲል ማለማመጥ አይከብደውም። ጥያቄውየህይወት ነው።
*
ዩስራ ትናንት ስለተቀደደውየክብሯ ማረጋ በሚውጠንጠን ማንባቷን ገ ትታዋለች። አሁን የእግር እሳት የሆነባት የወንድሟእና የዘቢባ ፍቅር እውቅና ሊነሳ መሆኑ ነው። ድሮ ህፃን ሆነው ወደ ቁርዓን ቤት ሲሄዱ ዩሱፍ እና ዘቢባ አንድ ሎሊፖፕ እየተቀባበሉ ለሁለት ይመጥጡየነበረበት ጊዜ አይኗ ላይ ድቅን አለ። ያኔ የሚገዙት ሶስት ሎሊፖፕ ነበር። አንዱ ለዩስራ ሁለቱ ደግሞለዘቢባ እና ለዩሱፍ። አንድ አንድ መጥባት እየቻሉ እነ ሱግን በየተራ አንዱን ለሁለት ይጠቡ ነበር። ታዲያ ዩስራ ስለምትቀና እሷንምእንዲያስጠቧት ብዙ ጊዜ ለምና አልተሳካላትም። ታዲያ ገና ከልጅነት የተማሰረተውከልብየማ ጨውየፍቅር ባርኮት ቅድስና ሊከለከል መሆኑን ማመን ለዩስራ ትልቅ ህመም ነው። መኝታ ክፍሏ ውስጥ ከጠረጴዛውፊት ለፊት ያለውወንበር ላይ ተቀምጣ ብሶቷን ለማመንጨር ሞከረች።
"ያንተን ፍቁድ ሚዜ ፣ በእሾህ ያልታጠረ፣
በእዝነትህ ትሩፋት ፣ በይሁን የተጨፈ፣
በሚልዕክትህ አድራሽ ፣ የተማከረ፣
ለማፍቀር በሽታ፣ ፈውስ ቢሆን ያሚረ፣
ከቶ ትዳር እንጂ፣ ሌላማምን አለ?
ምንምባይኖር ውሉ ፣ የሚያስከለክለው፣
ከትዳር 'ሚያሳቅብ፣ ማስፈርት ባይከልለው፣
ባላጠርከውሜዳ ፣ ዙሪያውእሾህ ዘረ፣
የፈቀድከውክልል ፣ ተከልክሎአደረ።
ስምፍረጃ ወጥተው፣ ባህል አሉት አጥሩን፣
ካንተ ሌላ ከልካይ ፣ ሚረቁት ሹመትን።
በአይሆኑ ፍረጃ ፣ ጉልበቱ ቢጠና፣
ፍቅር ሚሀል ገባ ፣ ትዳርን ገፋና።

.
ያነ ባሉ እነ ሱ
በባህል አለንጋ ፣ ፍቅራቸውተቀጥቶ፣
ይቁነ ጠነ ጣሉ
ያንተን የፍቃድ ቃል ፣ የሚያስፈፅምጠፍቶ።
ባንተ ላይ ተሾመ፣ ነገሰ ባህሉ፣
ተከልክሎአደረ ፣ ነፃ የነበር ሁሉ።
አንድ በለውሹመኝ ፣ ገፋፋኝ አመፁ፣
ወንጀል ሊከቱኝ ነው፣ ችለውላያነ ፁ!!"
በግጥሙየነ ዘቢባን ብሶት ዘረገፈችው። ሁሌምውስጧየሚታመቀውን ጭንቀት በዚህ ሜኩ ማውጣት ይቀላታል። ዩስራ ግጥሙን ፅፋ ስትጨርስ ዘቢባ ክፍል ሄዳ አነበበችላት። ዘቢባ ግጥሙውስጥ የተገለፀውየባህል አምባገነ ንነ ትየሚያከትምበት ጊዜ ናፈቃት። ተነ ስታ ወደ እናቷ ሄደች። ከወ/ሮ ጀሚላ ጋር ተቀምጠውየሚያወሩት እናቷ ፊት ተንበርክካ "እማ" አለች።
ፊቷ ላይ የተሳለውተስፋ መቁረጥ እየተነበባቸው"ምን ሆንሽ?" አሉ።
"አላግባ ይቅርብኝ! ግዴለሽምትንሽ ተረጋግቼ ዩሱፍ ባይሆን እንኳ ሌላ ሰውአገባለሁ። " አላሚው ጊዜ መግዛት ነበር።

ወ/ሮ ከንዚያ "ተይ ባክሽ! የናንተ አሻጥር ደሞይጥፋን እንዴ?" አሉ። ከዩሱፍ ጋር ተማክረውያማጡት ሀሳብ እንደሆነ ጠርጥረዋል።
"እማበአላህ? በቃ እንዳስከፋሽ አልፈልግም፡ ትዕዛዝሽን እያከበርኩ አይደል አንቺምተረጂኝ!"
"ተይ ተይ! ምንምየ ሜቀየር ነገር የለም! ሰውጠርተናል በቃ!"
ዘቢባ ንዴቷ ጣራ ነካ። "አላገባም! አባዬ ቢኖር ኖሮ እንዲህ አትጨዉቱብኝምነበር!" ብላ
እየተንሰቀሰቀች ወደ ክፍሏ ሮጠች። ሁሉምነገር የጨልመማሳላት። "ጌታዬ ሆይ እርዳታህ ወዴት
አለ?" የክፍሏን ጣሪያ እያየች ተማፀነች።
*
ዛሬ የኢድሪስ እና የዘቢባ ኒካህ የሜታሰርበት ቀን ነው። ዘቢባ ዩሱፍ ላይ እጅግ በጣምአዝናለች።
የሷ ምኞት "ይዞኝ ይጠፋል!" የሚል ነበር። ዩሱፍ ከኢድሪስ ጋር ያደረጉት ውይይት አለማካቱ
አብግኖታል። የኢድሪስ ሜልስ "እኔ ምእወዳታለሁ!" ነበር። ዩሱፍ ዛሬን ቤት ሜሆን ስላልፈለገ
ከሰሚር ጋር ኹሉድን ወደ ቁርዓን ህክምና ወስደዋታል። ወደ ሰባት ተኩል ገደማኢድሪስ ከቤተሰቦቹ
እና ከአጃቢዎቹ ጋር በአንድነት ማጡ። በዘቢባ በኩል የተወከሉት የዩሱፍ አጎት አቶ ከሚል ነበሩ።
የኒካህ ስነ ስርዓቱ ተጀምሮ የሰፈራቸውኡስታዝ ከጋብቻ ጋር የተያያዘ አጠር ያለ ንግግር አደረጉ።
ንግግሩ ሲያበቃ ዘቢባ ጥሎሽ ተጠየቀች። ጥሎሿን ከሷ ውጪየ ሚውስን ማንምየለምና ጋብቻውን
ለማጣጣል ማሳሪያ ልታደርገውተዘጋጅታለች። "አንድ ሚሊየን ብር!" በልቧ እሺ እንዳይል ፈጣሪዋን
ተማፀነች። ኢድሪስ በጣምደነገጡ። እየቀለደች ማሰለው።
እየተንተባተበ "አንድ ሚሊየን ለጥሎሽ?" አለ።
እንድትቀንስ ቢማፀኗትምፍንክች አልል አለች። ወ/ሮ ከንዚያና ወ/ሮ ጀሚላ ጋብቻውሊወድቅ ሚሆኑ
ሲገባቸውዘቢባን ለማቆጣት ሞከሩ። ዘቢባ ግን ፈቀቅ እንኳ ለማለት አልፈቀደችም፡
ወ/ሮ ጀሚላ እና ወ/ሮ ከንዚያ የነበራቸውብቸኛ አማራጭአምስት መቶ ሺህ ብሩን እነሱ ደጉመውት
ግማሹን እሱ ችሎ ጋብቻውን እንዲቀጥል ሜድረግ ነበር። ኢድሪስ ግን ውስጡእጅግ ስለተረበሸ
ጋብቻውን ትቶ ከሜድ ውጪየ ሚያስበውነገር አልነበረም፡
"ጋብቻውን ትተነዋል!" ኢድሪስ እንደምንምየተነፈሳት የሜጨረሻ ቃል ነበረች።
ዘቢባ ልቧ በሀሴት ተሞላ። አሸነፈች። ምንምዩሱፍ የፈለገችውን ያክል ባይታገልምማንምሊቀማት
በሜይችለውየ ጥሎሽ ማብቷ አማካኝነት የ ማትፈልገውን ሰውከማግባት ዳነች።
*
ሰሚር እና ዩሱፍ ኹሉድን የወሰዱበት የቁርዓን ህክምና ማዕከል ውስጥ ያሉት ሀኪሞች የቁርዓን
ህክምናውን ሜድረግ ጀምረዋል። ኹሉድ ሜሬቱ ላይ ትንፈራፈራለች። ሰሚር ሜሬቱ እንዳይጎዳት
በማስብቀና ሊያደርጋት ይጥራል። ህክምናውጥቂት ሰዓታት እንደፈጀ ድግምቱን የሰራውሁሴን
ሜሆኑን በአንደበቷ የሚያወራውጅኒ ተናገረ።
"እወዳት ነበር። ሰሚር ሜህላችን ገብቶ ባይነ ጥቀኝ እኔ ነበርኩየማገባት። ከሰሚር ጋር ሲጋቡ
ያለኝ አማራጭትዳራቸውን ሜበሽ ስለነበር ነውድግምቱን ያሰራሁባት።" ጅኒ ውሁሴንን ወክሎ
ይለፈልፋል።
ሰሚር ጅኒውየ ሜናገረውን ነገር በተግባር ተሚልክቶታል። አብረውሜተኛት እንዳይችሉ አድርጎ
በማካከላቸውቅራኔ ለሜፍጠር ይታገል እንደነበር አስታወሰ። ሁሴን ቤት የሄደችውበፈቃዷ
አለሜሆኑን ሲረዳ ያኔ የሰነዘረውጥፊ ራሱን አሜመው። ብዙዎች ጀግና አለሜሆናቸውየ ሚረጋገጠው
በንዴት ሰዓት በሚያሳዩት ራስን የ ሜቆጣጠር ድክሜት ነው። አንድምቀን በክፉ አይቶት የሚያውቀውን
የኹሉድን ፊት እንዲሜታ እና እንዲገፈትራት ያደረገውን ክስተት ከልቡ ጠላው። ሁሴንን ስለሜቅጣት
አሰበ።
የቁርዓን ህክምናውእንደተጠናቀቀ ሀኪሜቢሮውውስጥ ለዩሱፍ እና ለሰሚር ስለተፈጠረውነገር
ሊነግር ጠሯቸው። ገብተውእንደተቀሜጡፈገግ ብሎሜናገሩን ጀሜረ።
"የዚህ አይነት ድግምት የተለሜደ ነው! ወሰድ ማለስ እያደረገ የ ሚስትህ ፀባይ እንዲቀያየር
የ ሚያደርግ ነው። ብዙዎች በእንዲህ ያሉ ምክንያቶች ትዳራቸውእና ቤተሰባቸውተበትኗል። እናንተ
በጊዜ ሁኔ ታውን ስለተረዳችሁትና ይዛችኋት ስለማጣችሁ ሜልካምአድርጋችኋል።" አለና ሰሚርን
እየተማለከተ "ሜኝታ ላይ የ ምታስቸግርህ እሷ ሳትሆን የተሰራባት ድግምት ነበር። ሁሌምእሷ ላንተ
ደስታ ማስጠት እንዳትችል ለሜድረግ ልክ ልትገናኛት ስትል ወሰድ ያደርጋትና ሜጥፎውሜንፈስ ካንተ
ጋር ግብግብ ይፈጥራል። ሌላውወደ ነገርከኝ ሰውዬ ቤት የ ምትሄደውእሷ አይደለችም፡ በተሰራባት

ድግምት ማስረት ሳትፈልግ ትሄዳለች። ሜዷን እሷምአታውቅም፡ በኋላ ላይ ሲሜልሳት ደግሞ ያለችበትን ቦታ ስትማለከት ትደነ ግጣለች "ማን አመጣኝ?" የሚል ጥያቄ ትጠይቃለች። እርግዝና እንዳይፈጠርምምክንያት የሆነ ውይኸውድግምት ነ ው። ለማንኛውምአሁን ቋጠሮውበአላህ ፈቃድ ተፈትቷል። ግን ህክምና ውን እየተማለሰች ለተወሰነ ጊዜ ማከታተል ስለሚኖርባት ካርዱላይ ባለው የቀጠሮ ቀን ይዘሀት ና!" አለና ኸሉድ ወዳለችበት ክፍል እያማለከተ "አሁን ይዛችኋት ሜድ ትችላላችሁ። እና ደግሞአደራ ሰላቷን በሰዓቱ ትስገ ድ!" አለ።
ሰሚር የሰውልጅ ክፋት እጅጉን እየገረመው፣ እያንዳንዱ ሚስቱን በክፉ የጠረጠረበት ቀን እየቀፈፈውኸሉድ ወዳለችበት ክፍል ሲገ ባ ፊቷ ላይ የጋብቻቸውቀን "ያንተ ልሆን ነ ውእኮ!" ብላ የተፍለቀለቀችበትን ፈገ ግታ ራሱን አየ ው። ከፊቷ ላይ አንዳች ግርዶ እንደተነ ሳ አማ ። ኸሉድ አይኖቹን እያየ ች "ሁቢዬ ይቅርታ!" ብላ እቅፉ ውስጥ ማሻጋ ማነባት ጀሚረች። ሰሚር እንባውን ማከልከል ተሳነ ው። ዘለላዎቹ ተሽቀዳደሙ ይቅርታዋ ከንቱነ ቱን አጎ ላበት። "ይቅርታ አድርጊልኝ ሀያቲ!" በሁለት እጆቹ ደረቷን ከደረቱ ልጥፍ አድርጎ አቅፏት ተንሰቀሰቀ። ቤታቸውላይ የተሰቀለው ጥቁር ማጋረጃ ሲቀደድ ተሰማው። ጆሮዋ ስር ተለጥፎ "ዛሬምነ ገ ምሁሌምእወድሻለሁ!" አለ።
*
ዩሱፍ በዘቢባ ጥበብእጅግ ተደንቋል። ግቢውውስጥየ ቆሙውማኪና ውውስጥ ከጎ ኑ የተቀማጡችውን ዘቢባን እየተማለከተ "ድሮምእኮ ተንኮላችሁ ከባድ ሚሆኑ ቀድሞተነ ግሮናል!" አለና ማሳቅ ጀሚረ። ካማጣለት ቸኮሌት ከአንዱእያጎረሰችው"ስማእንዳንተ ቢሆንማያ ፈሪ አግብቶኝ ነበር። የሆንክ ቦቅቧቃ!"
"ማ ውቦቅቧቃ?" ሊማታት ሲል ከማኪና ውወርዳ አማለጠችው። ወርዶ በማኪናውዙሪያ ሚሯሯጥ ጀሙሩ። ወ/ሮ ከንዚያ የፎቁ በረንዳ ላይ ቆሙውድርጊታቸውን ተማለከቱና ፈገ ግ አሉ። የጨከኑበትን ፍቅር ጥንካሬ ሲያዩት ተረቱ።
ዩስራ ቸኮሌት ለማስረቅ ወደ ዩሱፍ ማኪና በሚሯሯጡት ተፈቃቃሪዎች ማሀል ሹልክ ብላ ስታልፍ ሁለቱም ፊታቸውን ወደ ጋራ ጠላታቸውአዞሩ። ወደ ቸኮሌት ቀሟኛዋ ዩስራ። እየተሯሯጡየ ሰረቀችውን ሊያስጥሏት ሄዱ። አሁን ሩጫውበሶስቱ ማካከል ሆኗል። ቤተሰቡ ውስጥያለውፍቅር ከረፈደ በኋላም ቢሆን ከከንዚያ ጋር ቆሙውለሚማለከቱት ለወ/ሮ ጀሚላ ምግልፅ እየ ሆነ የማጣይማላል።
ወ/ሮ ከንዚያ አይናቸውበሚሯሯጡት ሶስቱ የቤቱ ድምቀቶች ላይ እንዳረፈ "ግድየ ለሽምልጆቻችን ይደሰቱ! ለቀባሪውግድ የለምልጆቻችን ይቀብሩናል። " አሉ። ባህሉን ጥሰውለሚውጣት ያቀረቡት ጥያቄ የሚፎርሰውን ማዛዝምሚቋቋሚያ ሚፍትሔያዘለ ነበር።
ወ/ሮ ጀሚላ "እኔ እኮ ሁለቱንምእንደ ልጄነ ውየ ማያቸውእንዴት ልጄን ለልጄልዳር?" የባህሉን ወቀሳ ዘለውስለ ራሳቸውማውራታቸውእሳቸውምለማጋፈጥ ሙቁረጣቸውን ያሳይ ነበር።
ወ/ሮ ከንዚያ ፊታቸውን ወደ ወ/ሮ ጀሚላ እየ ማለሱ "እኛ እንደዛ ብናያቸውምእነ ሱ እንደዛ አልተያዩ ማ ፍቅር ተፈጥሮ ነ ው። ካልፈቀድንላቸውግን ዘቢባ ጥሎሿን እየቆለለች ሳታገ ባ ሚርጀቷ ነ ው!" አሉ።
"እንግዲ ካልሽ ይሁን! ካንቺ የሚቀርበኝ ወዳጅ የለም፡ በልጆቻችን ሙተሳሰር ቅርበታችን ቢጠነ ክር እንጂ አይላላም፡ በቃ ይሁና!" ወ/ሮ ጀሚላ የታሰሩበትን የባህል አጥር ሰብረውነ ፃ ወጡ። ይህ ነ ፃነ ት የሁለቱ ተፈቃቃሪዎችምነ ፃነ ት ነ ው።
ግቢውውስጥ ሲሯሯጡየ ነ በሩት ተፈቃቃሪዎች ዩስራን በቁጥጥር ስር አውለውየ ዘረፈችውን ቸኮሌት ሆዷ ጋር ካለውየ ሹራቧ ኪስ ውስጥእያራገ ፉ ነ ው። ወ/ሮ ከንዚያ ድምፃ ቸውን ከፍ አድርገ ው"ስሙ እናንተ ጦጣዎች! እንደናንተ ቆንጆ የሆነ ልጅ እንድታሳቅፉን አደራ!" አሉ። ዩሱፍ እና ዘቢባ የሰሙትን ለማምነ ተቸገ ሩ። ወ/ሮ ጀሚላ ለማስረገ ጥ በሚማስል ድምፅ "ሰርጉን በጥቅምት ብናደርገ ው ይርቃል?" ጥያቄ አለሚሆኑ ግልፅ ነ በር።
ዩሱፍ የዘቢባን አይን እያየ "አላህ ማላ አያሳጣንምአላልኩሽም? አየ ሽውጉልበቱን?" አለ። እናቱን ጥሎ ሳይጠፉና ሳያዝኑበት ዘቢባን የራሱ ሊያደርግ ሚሆኑ እጅግ ደስ አሰኘው።
ዘቢባ ምንምማለት ስላልቻለች አነ ባች። አንዳንዴደስታ ከቃላት ጋር አልገ ጥምይልና ከእንባ ይዛ ሙዳል። ደስስስ አላቸው። ዩስራ ሁለቱንምበአንድነ ት እያቀፈች "በሉ ደግሞአናታችን ላይ ውጡ" ብላ ስቃ አሳቀቻቸው። የፍቅር ደሙና ቤታቸውን አጠለለው። ፍቅር ዘነ በ።
***
የ ሜጨረሻውክፍል ይቀጥላል

ግርዶ

የ መጨረሻው ክፍል♥□♥□

ክፍል አስራሁለት (12)

.

<<ከሁለት ዓመት በኋላ!>>
መካኒሳ የ ሚገኘው የ ነ ዩሱፍ ቤት ውስጥ አንድ ህፃን የ ዩስራ መኝታ ክፍል ውስጥ ድክ ድክ እያለ ይራመዳል። ዩስራ "አሚኮ ቡቡቡቡቡ" እያለች ህፃኑን ለማጫወት ትሞክራለች። ቀኑ ቅዳሜነ ው። ዘቢባ ማስገጃዋን እያጠፈች "አጭውተሽ ሞተሻል። ይኼኔ በውስጡምኗ ሞኝ ናት እያለ እየፎገረሽ ነ ው" አለቻት።
"ነ ይ ውሰጂልኝ አሁን ላንብብበት ሰኞ ፈተና አለኝ!" ዩስራ ማጫወቱ ስራ ሆኖባታል።
ዩስራ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ ህክምና ትምህርት ቤት የ ሁለተኛ ዓመት ትምህርቷን እየ ተከታተለች ነ ው።
ዘቢባ ልጇን አስተኝታ ተመልሰችና "ስሚደግሞይኼየ ምትወጂውቆርቆሮ አዲስ ጩኸት ለቀቀ እኮ!" አለች። ዘቢባ ዩስራ አሁንምነ ሺዳ እንደምትወድ ስለምታስብ እያጣጣለች ልታበሽቃት ትሞክራለች።
"ተይውባክሽ!" ዩስራ ችላ አለቻት።
"እረ ምነ ውሲያገ ባ ደበረሽ እንዴ? የ ላጤነ ሺዳ ካልሆነ አትሰሚም?"
ኢስሚኤል ካገ ባ ስድስት ወር ገ ደማእንደሚሆነ ውዩስራ ታውቃለች። አገ ባ ሲባል ገ ርሟት ነ በር። ምናልባት ራሱን በአንድ ሊቆጥብ ከሆነ ትልቅ ለውጥ ነ ውብላ አድንቃለት ነ በር። በውስጧግን አሁንምበ ጋብቻውላይ ሽፍጥ የ ሚሰራ እየ ማሰላት ትጠረጥረዋለች። ላለፉት ሁለት አመታት ለኢስሚኤል ከመፀለይ የ ቦዘነ ችበት ቀን የ ለም። ወንጀሉን ተረድቶ ከጥፋት እጁን እንዲሰበስብ ፈጣሪ ልብ ይሰጠውዘ ንድ ተማፅናለች።
ዘቢባ ዩስራ ዝምስትላት "ለማንኛውምዩሱፌን ማታ የ ነ ሺዳውን ሲዲ ገ ዝተህ ና ብዬዋለሁ። እኔ ስማጣ ልገ ዛ ብዬ ረሳሁ። " ብላ ወጣች።
ዛሬ ሰሚር እና ኹሉድ እራት ተጠርተዋል። እነ ዩሱፍ በየ ወሩ እንዲህ ያለ ዝግጅት እያሰናዱ ትስስራቸውን ለማጥበቅ እየ ሞከሩ ነ ው።
አመሻሹን ዩሱፍ ወደ ቤት ሲመለስ ማስጂድ በር ላይ ካለች አንድ ትንሽዬ የ መፅሀፍት እና የ ሲዲ ማሻጫ የ ኢስሚኤልን አዲሱን የ ነ ሺዳ አልበምገ ዛ። አርዕስቱ "የ ፀፀት እንባዎች" ይላል።
ምሽቱን ወ/ሮ ጀሚላ እና ዘቢባ ባዘ ጋጇቸውበርካታ ምግቦች ሰሚር እና ኹሉድን ሊያስተናግዱ ሱፍራውን በአይነ ት በአይነ ቱ ሞሉት። ዩስራ ፈተና ስላለባት በጥናት ተወጥራ በምግብ ዝግጅቱ አልተሳተፈችም።
ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲል ዩሱፍ ሰሚርና ኹሉድን ይዟቸውመጣ። በቤታቸውመካከል ያለውርቀት ብዙምባይሆንምሌላ የ ትራንስፖርት አማራጭስለሌለ እንዳይቸገ ሩ በማሰብ ነ በር ቀድሞሄዶ ያመጣቸው።
ኹሉድ የ አንድ አመት እንደሷ ውብ የ ሆነ ች ሴት ልጇን እያጫወተች ለማዱ ቀረቡ። ዩስራ ምግብ መቅረቡን ሰራተኛቸውሰሚራ ሹክ ስትላት ወደ ሳሎን ሄዳ ተቀላቀለቻቸው።
"እ ሆዶ ለምግብ ሲሆን ጥናቱ ይቋረጣል አይደል?" ዘቢባ ዩስራ ገ ና ከማማጣትዋ አሾፈችባት።
ዩሱፍ ዩስራን ሲያይ የገ ዛውየ ነ ሺዳ አልበምትዝ እያለው"ፀፀት ምናምን የ ሚል ሲዲ አለ ክፈቸው እስኪ!" አላት። ዩስራ ሲዲውን ማጫወቻውውስጥ ስትከተውየ ኢስሚኤል ውብ ድምፅ ማስረቅረቅ ጀሚረ። ሰሚር የ ነ ሺዳውመጀሚሪያ ላይ የ ሰማውድምፅ እየ ገ ረመው"ቆይ ኣኣኣ ኡኡኡ ምናምን ካላሉ ነ ሺዳውን አይጀምሩምእንዴ? አሁንስ ቢስሚላህ አስማሉት እኮ!" አለ። ከዩስራ በስተቀር ሁሉምሳቁ።
ዩስራ የ ነ ሺዳውን ግጥምስትሰማማነ ባት ጀሚረች።
"አነ ባለሁ፣ ጩኸቋት ነ ፍሴ፣
ሰላምአጣሁ፣ በሚረከሴ።
ፈተና ነ ው፣ ብለህ ነ ግረህ የ ፈተንከኝ፣
ስወድቅበት፣ ስዘቅጥበት ያልታወቀኝ፣

ተደራርቦ ሰማይ ነካ፣
ለጥፋቴ እሳት ቦካ።
ሊጋገር ነውከገላዬ፣ የእሳት ማማ፣
የኔ ኑሮ፣ ከትዕዛዝህ አልተስማማ፡
ምክኒኑን ነፍስ፣ ከአዘቅት ጣልኩት፣
ያማኝን ከመንገድህ አሳሳትኩት።
ባንተውሹመት፣ አመፅኩበት፣
እልፍ ጩዋን፣ ጩቆንኩበት።
አነባለሁ፣ ጩኸቋት ነፍሴ፣
ሰላምአጣሁ፣ በሞኚከሴ።
ከክብራቸውሲናጡ፣ በኔ አለንጋ፣
ውብቀናቸውሲጨልልም፣ ልቤን ወጋ።
ከውጉ ስር ከፈሰሰ፣ ጥቂት ኩራት፣
የእኔነቴን ትንሽነት፣ አየሁባት።
ምናለ አልኩኝ
ባልገረፈ አለንጋዬ፣ ያንን ገላ፣
ለትዕዛዝህ የወደቀን፣ ባላጉላላ።
በሹመትህ ባልቀበጠ፣ ያንተን ክብር ባስተዋለ፣
የያዝከውን ቀን፣ የሚያድነውእንደሌለ።
ምን ነበረ? ምን ተሻለ?
ያቆሰልኩት፣ ያደማሁት ብዙ አለ።
አነባለሁ፣ ጩኸቋት ነፍሴ፣
ሰላምአጣሁ፣ በሞኚከሴ።
ይቀርታነውየምላምን፣ ከተጎዱ፣
ካንተ ሽተው፣ እኔን መሞር ከወደዱ።
ይቅር ካሉኝ፣ ከነፃሁኝ ከሰውእዳ፣
በእዝነት ወንዝህ እጠብነፍሴን፣ ውስጤይፅዳ።
እንባ በዛ ተማላጠሽፋሽፍቴ፣
በሹመትህ፣ በመቅጣቴ፣
አነባለሁ፣ ጩኸቋት ነፍሴ፣
ሰላምአጣሁ፣ በሞኚከሴ።
ፈተና ነው፣ ብለህ ነግረህ የፈተንከኝ፣
ስወድቅበት፣ ስዘቅጥበት ያልታወቀኝ፣
ተደራርቦ ሰማይ ነካ፣
ለጥፋቴ እሳት ቦካ።"
ዩስራ ያደረገችውፀሎት ማስሙኑ ደስ አሰኛት። ፈጣሪዋን አማስገነች። ዘቢባ የዩስራን ማንባት ተሜልክታ "ሰውበቁርዓን ያለቅሳል አንቺ በነሺዳ! አላህ ይሁንሽ!" አለች። ዩስራ ነቆራዋ ስለገባት ፈገግ ብላ አለፈቻት።
እራት ተበልቶ እንደተጠናቀቀ ዩስራ ወደ ማኝታ ክፍሏ ሄዳ ኢስማኢል ጋር ደወለች።
"ዩስራ!" ኢስማኢል ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ ተቀበላት።
"ነሺዳህን ሰማሁት! አሁን የእውነት የተፀፀትክ ይማስላል!"
"አዎን እጅግ ፀፅቶኛል። እባክሽ ይቅር በይኝ?"
"እኔ ይቅር ካልኩህ ቆይቻለሁ። አላህ ይቅር ይበልህ!"
"በጣምአማሰግናለሁ ዩስራ!"
ተሰነባብተውስልኩተዘጋ። የሱን ነውር የሸፈነውፈጣሪዋ የሷንምጉድ እንዲሸፍነውበልቧ ለማች።
የእራት ስነ ስርዓቱ ተጠናቆ ዘቢባ እና ዩሱፍ እንግዳዎቻቸውን ቤታቸውለማድረስ ተነሱ። ዩሱፍ እየነዳ ዘቢባ እና ኹሉድ ከኋላ ገብተውሰሚ ጋቢና ተቀምጧል። የነዩሱፍ ሰፈርን ቅያስ ወጥተው

ወደ ኮንደሚኒየም መግቢያ ጋር ሊደርሱ ሲሉ አንድ የተቀዳደደ ልብስ የለበሰና ፀጉሩ የተንጨበረረ ጎረምሳ ከራሱ ጋር እየጮኸ ሲያወራ ተመለከቱት። ሁሴን ነበር። ድግምቱ ከከሸፈ በኋላ ወደ እሱ ዞሮበት አብዷል። ሰሚር ሁሴንን እያየ "ድግምት ወደ ደጋሚው ዞረ ማለት ይሄ ነው እንግዲህ!" አለና "አላህ ይዘንለት!" አለ። ሁሴን ካበደ አንድ አመት ገደማ ሆኖታል። ንብረቱ ሁሉ በሰራተኞቹ ተበልቶ ከስሯል። "ኸሉዴ አለች እሷ እኮ የምድር አምላክ ነች ..." ሁሴን ብቻውን ይቀባጥራል። ሚኪናው ሁሴንን አልፎ ወደ ኮንደሚኒየም መግቢያ በር ፈሰሰ። ሰሚር እና ኸሉድን ብሎካቸው ጋር አድርሰው ዘቢባና ዩሱፍ ተመለሱ።

ኸሉድ እና ሰሚር የሚወዱትን የአልጋ ላይ ትግላቸውን ለማካወን በአይናቸው ተግባብተው ወደ ቤታቸው ተቻኮሉ። የታቀፈችው ህፃን ችኮላቸው የገባት ይመስል "ኣኣ ሀሀ ይይ" ብላ አሽሟጠጠች።

ዩሱፍ እና ዘቢባ ቤት ሲደርሱ ዩስራ ግጥም እየሞነጨረች ነበር። አንድ ቀን ከነ ማንነቷ ተቀብሎ የሚያገባት ሰው እንደሚመጣ በፈጣሪዋ እርግጠኛ ናት።

የፃፈችውን ግጥም ትኩር ብላ አየችው፡

"የሰበረኝ መዶሽ ፣ ባንተ ከታቀበ፣
ክፉው የጥፋት እጅ፣ ከተሰበሰበ፣
ስብራቴ እንዲድን ፣ እንዲሽር ህመሜ
መዶሹን ባቀብከው፣ ይጠገናል ቅስሜ፡
ወዲህ በል ግጣሜን ፣ ልሰካ ከጎኑ፣
ይፈወስ ህመሜ፣ ላማስግን አንተኑ።

ልፈወስ ነ ውማነል ፣ ተረጋጋ ልቤ፣
ማነ ን ነ ውየ ላ ከ ው፣ ልጠብቅ ተውቤ። " ግጥሙአ ል ጥምሲላ ት ቀደደችው፡ "አ ን ድ ቀን ለኔ የ ሚ ጥከ ው ሰ ው ያ ገ ባ ኛ ል! ያ አ ን ድ ቀን እ ስ ኪደ ር ስ በ ትዕ ግስ ት እ ጠብቃለ ሁ!" ለ ራ ሷ ተና ገ ረ ች። ውስ ጧአ ዳ ማጣት ማነ ል ፈገ ግ አ ለ ች።
***
ተፈ ፀ ሟ!